3. *መልስህ ከዚህ በታች ከሰፈሩት ጋር ተመሳሳይ መሆን አለበት*

ሀ. አናሲሞስ ከእርሱ ኮብልሎ የሄደና ምናልባትም የእርሱን አንዳንድ ንብረቶች ሰርቆ ይሆናል (15፣18)።
ለ. ጳውሎስን ራሱን እንደሚቀበለው እናሲሞስን እንደ ወንድም እንዲቀበለው ፊልሞናን ጠየቀው (16-17)
ሐ. የጳውሎስ ልመና መሠረቱ ፍቅር ነው። (9)
መ. ብድር ያለበት ከሆነ ጳውሎስ ለመክፈል ፈቃደኛ መሆኑን በመግለጽ በእርሱ ላይ እንደሆነ አድርጎ እንዲቆጥረው ነገረው (19)።

9. (*መልስህ ከዚህ ጋር ተመሳሳይ መሆን አለበት*) በችግሮቹ ተካፋይ ሆኑ (14)፣ በተሰሎንቄ በነበረ ጊዜ እርዳታ ላኩለት (16)፣ በእስር ቤት በነበረ ጊዜ ስጦታዎች ላኩለት (18)።

4. ሀ እና ሐ

10. *መልስህ ከዚህ ጋር ተመሳሳይ መሆን አለበት*፦

በመልእክቱ ውስጥ ያስገባው ለፊልጵስዩስ ሰዎች ራስን ዝቅ የማድረግ ምሳሌ ለመስጠት ነው።

5. *መልስህ ከዚህ በታች ከተዘረዘሩት ጋር ተመሳሳይ መሆን አለበት*።

አመጣጣ፦ ምሳሌውን ተመልከት።

ኃይሏ፦ እግዚአብሔር ከርስቶስን ለማስነሣት የተጠቀመበት ኃይል ዓይነት።

ማሕተሟ፦ መንፈስ ቅዱስ።

ራሷ፦ ክርስቶስ።

መሠረቷ፦ ክርስቶስ መሠረታቸው የሆነው ነብያትና ሐዋርያት።

ሕይወቷ፦ መልካም ሥራዎች፣ ፍቅር፣ ብርሃንና ጥበብ።

ጠላቷ፦ በምድርና በሰማይ ያሉ የክፉት መንፈላውያን ኃይላት።

የሙር ዕቃዋ፦ የእግዚአብሔር የሙር ዕቃ ሁሉ፣ እውነት፣ ጽድቅ፣ የሰላም ወንጌል፣ እምነት፣ ድነትና የእግዚአብሔር ቃል።

11. ሀ፣ ለ እና መ

8 የቤተክርስቲያን መፍትሔዎችን ማግኘት

ትምህርት

በስባተኛው ክፍለ ትምህርት ጳውሎስ በእስር ቤት ሆኖ የጻፋቸውን የእስር ቤት መልእክቶች ስናጠና እያንዳንዱ መልእክት ስለ ከርስቶስና ስለ ቤተክርስቲያን እውነቱን እንዴት እንደሚያብራራ ተመልክተናል። እነዚህ መልእክቶች ስለ ጳውሎስ ባሕርይና አገልግሎትም ጠለቅ ያለ ግንዛቤ እንድናገኝ አድርገውናል። በተጨማሪም ጳውሎስ በሮም በታሰረበት ወቅት በተለያዩ ስፍራዎች የነበሩ አብያተ ክርስቲያናት እንዴት እያደጉ እንደሄዱ ከእነዚህ መልእክቶች ለመረዳት ችለናል።

በዚህ በስምንተኛው ክፍለ ትምህርት የምንመለከተው ከጳውሎስ የመጀመሪያው የሮም እስር ቀጥሎ ባሉት ዓመታት ውስጥ የተጻፉትን አምስት መልእክቶች ይሆናል። በእነዚህ ዓመታት ቤተክርስቲያን እያደገችና እየተስፋፋች መሄዷን ብትቀጥልም፣ ተቃውሞና መከራም እያደገና እየጠነከረ የሄደባቸው ዓመታት ነበሩ። በክርስትና እምነትና በአይሁድ ሃይማኖት መካከል ያለው ግንኙነትም በማያጠራጥር መንገድ ውሳኔ ማግኘት ያስፈለገው ወቅት ነበር።

በእነዚህ ጉዳዮች ላይ የእግዚአብሔር መንፈስ መመሪያንና ጥበብን እየሰጠ በሄደ ቁጥር የቤተ ክርስቲያን መሪዎችም ተገቢውን ምላሽ ይሰጡ ነበር። ለቤተክርስቲያን መሪዎች መሟላት ያለባቸው አንድ ዓይነት የሆኑ መደበኛ ሥርዓቶች ተወሰኑ። ስለ ለደት ክርስቲያናዊ የሆነ አመለካከት እንዲኖር በዚህ ጉዳይ ላይ የክርስቲያኖች ዝንባሌ እንዴት መሆን እንዳለበት ተብራራ። የአይሁድ ሃይማኖት አስፈላጊነትን በተመለከተም እግዚአብሔር በክርስቶስ ከለጠው መገለጥ አንጻር ግለጻ ተደረገ። ቤተ ክርስቲያን በዚህ ምክንያት እየተጠናከረች በመሄዷ የራሷ የሆነ ድርጅታዊ መዋቅር መዘርጋት ጀመረች።

የክፍለ ትምህርቱ አክፋፈል

- ለእድገት የተሰጠ ምላሽ፡ ለጢሞቴዎስና ለቲቶ የተጻፉ መልእክቶች፡
- ለሰዶት የተሰጠ ምላሽ፡ የመጀመሪያው የጴጥሮስ መልእክት፡
- ለእይሁድ ሃይማኖት የተሰጠ ምላሽ፡ ወደ ዕብራውያን የተጻፈ መልእክት

የክፍለ ትምህርቱ ዓላማዎች

ይህን ክፍለ ትምህርት ስትጨርስ ከዚህ የሚከተሉትን ማድረግ መቻል አለብህ፦

- ስለ ጳውሎስ ሕይወት የመጨረሻ ዓመታት፣ ስለ ጢሞቴዎስና ስለ ቲቶ እገልግሎት እዲስ ኪዳን የሚያሳየውን መግለጽ፤

- ጳውሎስ ለጢሞቴዎስና ለቲቶ በጻፈው መልእክቶች መሠረት የመጋቢነት እገልግሎት ዓላማና ግቦችን መግለጽ፤

- ስመጀመሪያው የጴጥሮስ መልእክት ውስጥ ስለ ስደትና ስለ መከራ፣ ስለ ክርስቲያናዊ ኑሮ የተሰጠውን ትምህርት ለይቶ ማወቅ

- ስዕብራውያን መልእክት ውስጥ የሚገኘውን፤ ክርስትና ከእይሁድ ጋር ስላለው ግንኙነት ያለውን አውነት ማብራራት።

የክፍለ ትምህርቱ *መመሪያዎች*

- ለዚህ ክፍለ ትምህርት የተሰጠውን እያንዳንዱን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ማንበብህን ካረጋገጥህ በኋላ የትምህርቱን ዝርዝርዝ እንደ ተለመደው እጥና።

- ወደ ጢሞቴዎስ፣ ቲቶና ዕብራውያን የተጻፉትን መልእክቶች የመጀመሪያውን የጴጥሮስ መልእክት ጭምር በተሰጠው መመሪያ መሠረት እንብብ።

- ክፍለ ትምህርቱን በሚገባ ካጠናህ በኋላ የጥናት ማጠናከሪያ ጥያቄዎቹን መልስ። ከዚያም ስትምህርቱ መጨረሻ ላይ ከተለጡት መልሶች ጋር በማስተያየት ስትክክል ያልመለስካቸውን አስተካክል። የመከራ ፈተናውን ከወሰድክ በኋላም እንዲሁ አድርግ።

የትምህርቱ ዝርዝር

ክፍለ ትምህርቱን የምንጀምረው በጳውሎስ ሕይወት በመጨረሻ ዓመታት የተከናወኑትን በማጥናት ነው። ከዚያም የእርሱ ተባባሪ ለነበሩት ለጢሞቴዎስና ስቲቶ የጻፋቸውን መልእክቶች እናጠናለን። ከዚያ በኋላ የመጀመሪያውን የጴጥሮስን መልእክትና ወደ ዕብራውያን የተጻፈውን መልእክት አንድ በአንድ እንመለከታለን። እነዚህ አምስት መልእክቶች የሚያሳዩን ከመጀመሪያው የጳውሎስ የሮም እስር በተከተሉት ዓመታት ቤተክርስቲያን በተነሱባት ችግሮች አንዴት መቋቋም እንደቻለችና መፍትሔ እንዳገኘች ነው።

ለዕድገት የሚሰጠ ምላሽ፡
ለጢሞቴዎስና ለቲቶ የተጻፉ መልእክቶች

ዓላማ 1 በመጋቢነት መልእክቶች ውስጥ የሚገኙትን የጳውሎስን ሕይወትና ያስተማራቸውን ትምህርቶች ለመግለጽ።

ጳውሎስ ለጢሞቴዎስና ለቲቶ የጻፋቸው መልእክቶች "የመጋቢነት መልእክቶች" በመባል የተጠሩት ጢሞቴዎስንና ቲቶን ስመጋቢነት አገልግሎታቸው ስማበረታታትና በእድገት ላይ ላለች ቤተክርስቲያን አስፈላጊውን መመሪያ ለመስጠት የተጻፉ በመሆናቸው ነው። እነዚህ መልእክቶች ጳውሎስ ተባባሪዎቹ ለነበሩት ምክር በመስጠትና የሚያጋጥማቸውን ከቤተክርስቲያን አድገት ጋር የተያያዙ ችግሮችን እንዴት መፍታት እንደሚችሉ የሚያሳዩ ከመሆናቸውም በላይ የጳውሎስን ተግባራዊ ጥበብ ይገልጣሉ።

ጳውሎስ ሩጫውን ፈጸመ

የሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ በሮም የጳውሎስ እስራት ውጤት ምን እንደሆነ ሳይገልጽ ያበቃል። ሆኖም ከነዚህ የመጋቢነት መልእክቶች ከተባሉት አንደምንረዳው፣ ጳውሎስ ከእስራት ለጊዜው እንደተፈታና እንደገና በአንዳንድ ስፍራዎች እንደተዘዋወረ ለመረዳት እንችላለን። በ2ጢሞ 4:16-17 ላይ ሲናገር፦ "በተከሰስሁበት ነገር ... ጌታ በእጠገቤ ቆሞ አበረታኝ ከእንበሳም መንጋጋ አዳነኝ" ይላል።

(1). ከዚህ በታች የተዘረዘሩት ጥቅሶች ጳውሎስ ከመጀመሪያው እስራቱ በኋላ ነፃ ሆኖ እየተዘዋወረ የነበኛቸውን ስፍራዎች የሚያመለክቱ ናቸው የነበኛቸውን ቦታዎች ስም በጥቅሱ ጎን አስፍር።

ሀ. 1ጢሞ1:3 _____
ለ. ቲቶ1:5 _____
ሐ. ቲቶ3:12 _____
መ. 2ጢሞ 4:20 _____
ሠ. 2ጢሞ 4:13 _____

ከሦስቱ የመጋቢነት መልእክቶች ውስጥ በመጨረሻ የተጻፈው 2ኛ ጢሞቴዎስ ነበር። ሐዋርያው ጳውሎስ መልእክቱን በጻፈበት ወቅት ተመልሶ እስር ቤት ገብቶ ስለነበር ብዙ ጊዜ እኖራለሁ የሚል ግምት አልነበረውም (2ጢሞ 4:6-7)። እንዳሰበውም ከዚያ በኋላ ጳውሎስ ብዙ ጊዜ እንዳልቆየና ወደ 64 ዓ.ም ገደማ በሮማዊው ንጉሥ በኔሮ እንደተገደለ ነው የምንረዳው።

(2). የመጋቢነት መልእክቶች የተባሉት ስለ ጳውሎስ የሚያመለክቱት የትኛውን ነው?

ሀ. ከመጀመሪያው እሥራቱ በኋላ ጳውሎስ በሮም ታግዶና ተወስኖ እንደኖረ
ለ. 2ኛ ጢሞቴዎስን በጻፈበት ወቅት ነፃ እንደሚለቀቅ እንዳሰበ
ሐ. እንደገና ከመታሰሩ በፊት መቄዶንያንና ሌሎችንም ስፍራዎች እንደጎበኘ

የጳውሎስ የአሟሟት ሁኔታ በእርግጠኝነት ባይታወቅም፣ በምድር ላይ ያሳለፈው ሕይወት ግን በደንብ ይታወቃል። እዳኙንና ጌታውን በደማስቆ መንገድ ላይ ከተገናኘበት ጊዜ እንሥቶ፣ እርሱን ከመውደዱ የተነሣ ራሱን ሙሉ በሙሉ ለጌታ አሳልፎ በመስጠት እርሱን ብቻ እያገለገለ ደስ የሚያሰኝና የድል አድራጊ ሕይወት ኖሯል። በአገልግሎት ላይ ባለ ብዙ ችግሮች ተፈራርቀውበታል። የመርከብ መስበር አጋጥሞታል፣ ተደብድቧል። በድንጋይ ተወግሯል። ተቃውሞና እስራት አጋጥሞታል። እነዚህ ሁሉ ቢፈራረቁበትም ጌታውንና አዳኙን በታማኝነት በመከተል የወንጌል እገልግሎቱን ለዓለም አበረከተ። በዚህም ምክንያት ወንጌል በሜዲትራንያን ዓለም ተሰብኮ አብያተ ክርስቲያናት ተቋቁመው። ሐዋርያውም መንፈስን የሚያነሳሳ ደስ የሚያሰኝ ምሳሌነቱን ትቶልን ሩጫውን በሚገባ ፈጽሞ ወደ ጌታው ሄደ።

የጢሞቴዎስ አገልግሎት

ጢሞቴዎስ ከአይሁድና ከአሕዛብ ዘር የተወለደና በሚያምኑት አማኞች ዘንድ የተከበረ ወጣት ሰው ነበር። (ሐዋ 16:1-3)። በሁለተኛ የወንጌል ጉዞው ላይ ጳውሎስ ጢሞቴዎስን ከእርሱ ጋር ከወሰደው ጊዜ እንሥቶ የማያቋርጥ አጋር ሆነው። ጳውሎስ በኤፌሶን ለሦስት ዓመታት በቆየበት ወቅት በሥራው ያገዘው ጢሞቴዎስ ሲሆን፣ በኋላም ከደርቤን ተወካዮች አንዱ በመሆን ከጳውሎስ ጋር ወደ ኢየሩሳሌም ተጉዟል (ሐዋ 20:4)። በቆላ 1:1 እና በፊል 1 ላይ የተጻፈው እንደሚያመለክተው በመጀመሪያው የሮም እስራቱ ወቅት ጢሞቴዎስ ከጳውሎስ ጋር እንደነበር ነው። ጳውሎስ ከእስር ከተፈታ በኋላ ወደ ኤፌሶን በመሄድ በዚያ የተጀመረውን መንፈሳዊ ሥራ የበላይ ተመልካች ሆኖ እንዲቆጣጠር ጢሞቴዎስን በኤፌሶን እንዲቆይ እድርጎ ወደ መቄዶንያ ሄደ (1ጢሞ1:3)። ከዚያም ጢሞቴዎስ ለመጨረሻ ጊዜ ከጳውሎስ ጋር የተገናኘው ጳውሎስ ከመሞቱ በፊት በሮም እንደነበር በ2ጢሞ 4:9፣21 ይገልፅልናል። በአንድ ወቅት ጢሞቴዎስ እስር ቤት ገብቶ እንደነበር በዕብ 13:23 ላይ የተጻፈው ቃል ይነግረናል።

የቲቶ አገልግሎት

ቲቶ ክርስቶስን የተቀበለው በአንጾኪያ ነው። አሕዛብን የመግረዝ ጥያቄ አከራካሪ ጉዳይ ሆኖ በተነሣ ጊዜ ጳውሎስ ስለዚሁ ጉዳይ ከመሪዎች ጋር ለመወያየት ቲቶን ይዞ ወደ ኢየሩሳሌም እንደሄደ ገላ 2:1-3 ላይ የተጻፈው ቃል ይነግረናል። በቆሮንቶስ ቤተክርስቲያን ችግሮች በተነሱ ጊዜ እንዳንዶቹን ችግሮች እንዲያቃልል ጳውሎስ ቲቶን ላከው። ቲቶ በዚህ ኃላፊነቱ ፍሬያማ ነበር (2ቆሮ 7:6-16)። ለችግሮች ቅዱሳን መርጃ የሚሆን መባ በመሰብሰብ ታላቅ አስተዋፅዖ ያደረገ አገልጋይ ነበር። ጳውሎስ ቲቶን የሚጠራው "አብሮ የሚሠራ የሥራ ጓደኛው" አድርጎ ሲሆን፣ በአብያተ ክርስቲያናትም ዘንድ ሁሉ ተወዳጅነት የነበረው የተመሰገነ አገልጋይ መሆኑን ከ2ቆሮ 8:6፣16-24 ለመረዳት እንችላለን። ጳውሎስ ከእስር ከተለቀቀ በኋላ ቀርጤስን በነበኘበት ወቅት አርጤማስን ወይም ቲኪቆስን እስኪልክ ድረስ በዚያ የተጀመረውን መንፈሳዊ ሥራ የበላይ ተቆጣጣሪ ሆኖ እንዲመለከት ቲቶ በዚያ እንዲቆይ ማድረጉን በቲቶ 1:5፣3:12 ላይ ከተጻፈው ለመረዳት እንችላለን። ጳውሎስ ሰሁለተኛ ጊዜ በሮም ሲታሰርም ቲቶ ለተወሰነ ጊዜያት በዚያ ሳይኖር እንደማይቀርና በኋላም ወደ ድልማጥያ እንደሄደ በ2ጢሞ 4:10 ላይ የተጻፈው ቃል ይነግረናል።

(3). መግለጫው የሚናገረው ስለ ጢሞቴዎስ ከሆነ፣ቁጥር "1" ስለ ቲቶ ከሆነ፣ ቁጥር "2" በተሰጠው ስፍራ በመጻፍ አመልክት።

_____ሀ. የቆሮንቶስ ቤተክርስቲያንን ችግሮች ለማቃለል የረዳ
_____ለ. በኤፌሶን የቤተክርስቲያንን ሥራ በኃላፊነት እንዲሰራ የተቀመጠ
_____ሐ. ከይሁድና ከአሕዛብ ወገን የነበረ
_____መ. ከደርቤን ተወክሎ ከጳውሎስ ጋር ወደ ኢየሩሳሌም የተጓዘ
_____ሠ. በቀርጤስ የቤተክርስቲያን ሥራ በኃላፊነት እንዲሰራ የተደረገ

አንደኛው የጢሞቴዎስ መልእክት

ጳውሎስ ከእስራቱ ከተለቀቀ በኋላ ወደ ኤፌሶን ሄዶ በዚያ ለተጀመረው መንፈሳዊ ሥራ ለጊዜው ጢሞቴዎስን በኃላፊነት አስቀምጦ ጉዞውን ወደሌላ ስፍራ አቀና። ወደ ኤፌሶን ለመመለስ አቅዶ ድንገት የሚያዘገይ ጉዳይ ከገጠመን በማለት ለጢሞቴዎስ ደብዳቤ መጻፉን በ1ጢሞ 3:14-15 ላይ ከተጻፈው ለመረዳት እንችላለን። ጳውሎስ ወደ ሌላ ስፍራ ከሄደ በኋላ ጢሞቴዎስ በኤፌሶን የነበረውን መንፈሳዊ አገልግሎት እንዴት እንደሚያ ካሂድ ግልጽ የሆነ መመሪያ እንዲኖረውና ለአገልግሎቱም የሚረዳውን ትምህርት ለመስጠት የመጀመሪያ መልእክቱን ወደ ጢሞቴዎስ ላከ።

(4). በ1ጢሞ 1:3-4 ጳውሎስ ጢሞቴዎስን በኤፌሶን እንዲቆይ ያደረገው

ሀ. ለተቸገሩ ቅዱሳን መባ እንዲሰበሰብ
ለ. አንዳንድ ሰዎችን የሐሰት ትምህርት እንዳያስተምሩ እንዲናገር

ሐ. በእካባቢው የነበሩ አማኞችን እንዲጠብኝ

በመልእክቱ መግቢያ ላይ ስለ ሐሰት ትምህርት አስተማሪዎች መግለጫ ከመስጠቱም በላይ፣ ከዚህ በታች በተዘረዘሩት ጉዳዮች ላይም አስፈላጊውን መመሪያዎች ለጢሞቴዎስ ሰጥቷል።

- ስለ እምልኮ *መመሪያ* ሰጥቷል (1ጢሞ 2፡1-15)
- ስለ ቤተክርስቲያን *መሪዎች መመዘኛ* ሰጥቷል (1ጢሞ 3፡1-16)
- ስለ *መበለቶች መመሪያ* ሰጥቷል (1ጢሞ5፡1-16)
- ለለ ቤተክርስቲያን *ሽማግሌዎች መመሪያ* ሰጥቷል (1ጢሞ 5፡ 17-22)
- ስለ *ባሪያዎች መመሪያ* ሰጥቷል (1ጢሞ 6፡1-2)
- ስለ ሐሰት ትምህርት ማስጠንቀቂያና ስለ ሐብት ከንቱነት *ማብራሪያ* ሰጥቷል (6፡3-10)
- ስለ *መንፈሳዊ* ሕይወቱና ስለ እገልግሎቱ አስፈላጊውን ምክር ሰጥቷል (1፡16-20፣ 4:1-16፣6፡11-21)።

መልእክቱ የሚያሳየው ጳውሎስ ከጢሞቴዎስ *ጋር* የነበረውን የቅርብ ግንኙነት ቢሆንም፣ የሰጠው ምክርና *መመሪያዎች* ግን በሥልጣን የተሞሉ ናቸው። ስለ ተማረው *መንፈሳዊ* ትምህርት በተደጋጋሚ እንዲያስታውስ ደጋግሞ ያሳስበዋል። (1፡16፣ 4:14፣6፡12፣20)። ከልጅነቱ ጀምሮ የተማረውን እንዲያስታውስ ያደረገበት ምክንያት ጢሞቴዎስ አስቸጋሪ በሆነ ሁኔታ ላይ እንዳለ ተስምቶት በአገልግሎቱ እንዲበረታና እንዲነቃቃ ለማድረግ ሳይሆን አይቀርም።

ወደ ጢሞቴዎስ የተጻፈውን የመጀመሪያውን መልእክት ከዚህ በታች የተሰጠውን አከፋፈል በመከተል እንብብ።

1ኛ ጢሞቴዎስ፡ ለእግዚአብሔር ሰው የተሰጠ *መመሪያ*

I. የግል ማስጠንቀቂያና ልመና	1:1-20 እንብብ
II. የቤተክርስቲያን *ሥርዓት መመሪያ*	2:1-3:16 እንብብ
III. የተለየ ምክር	4:1-16 እንብብ
IV. የእርስ በርስ ግንኙነት *መመሪያ*	5:1-6:2 እንብብ
V. የመጨረሻ ምክርና አደራ	6:3-21 እንብብ

(5). ጳውሎስ ለጢሞቴዎስ የሰጠውን አደራ 1ጢሞ 6:11-16 ላይ ካነበብክ በኋላ የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልስ በማስታወሻ ደብተርህ አስፍር።

ሀ. ጢሞቴዎስ መሸሽ ያለበት ከምን ነበር? (6:3-10)
ለ. ጢሞቴዎስ መከተል ያለበት ምን ነበር? (ቁ.11)
ሐ. ጢሞቴዎስ መዋጋት ያለበት ምን ነበር? (ቁ.12)
መ. ጢሞቴዎስ *መያዝ* ወይም መጠበቅ ያለበት ምን ነበር? (ቁ.12፣14)

በዚህ *መልእክት* የእግዚአብሔር አገልጋይ ለነበረው ለወጣቱ ጢሞቴዎስ የተሰጡት *መመሪያዎችና* ምክሮች እንደዚሁም ማስጠንቀቂያዎች ዛሬም በዚህ ዘመን ላሉ እገልጋዮች አስፈላጊነታቸው ከፍተኛ ነው። ጌታን በታማኝነት ለማገልገል የሚፈልግ ሁሉ በጥንቃቄ ሊያጠናቸውና በተግባር ላይ ለማዋል ተገቢውን ጥረት ሊያደርግ ይገባል።

ወደ ቲቶ የተጻፈው መልእክት

ጳውሎስ የመጀመሪያውን *መልእክት* ወደ ጢሞቴዎስ ከጻፈ በኋላ ወደ ቀርጤስ የተጓዘ ይመስላል (ቲቶ 1:5)። በቀርጤስ ደሴት ላይ ብዙ ክርስቲያኖች ነበሩ። እነዚህ አማኞች በመጀመሪያ ወንጌልን የሰሙት በበዓለ *ሃምሳ* ዕለት በኢየሩሳሌም ከተማ ከተገኙት *መንገደኞች* ሊሆን እንደሚችል ይገመታል (የሐዋ 2:11)። ጳውሎስ በእነዚህ አማኞች *መ*ካከል ለተወሰነ ጊዜ ካገለገለ በኋላ፣ በዚች ደሴት ላይ የተጀመረውን *መንፈሳዊ ሥራ* እንዲያደራጅና እንዲያጠናክር ቲቶን በዚያ እንዲቆይ አድርጎ፣ ሐዋርያው ወደ ሌላ ስፍራ ጉዞውን አቀና (ቲቶ 1:5)። የቲቶ ተግባር ቀደም ሲል የተደራጀውን *መንፈሳዊ ሥራ* በኃላፊነት እንዲመራ ከተመደበው ከጢሞቴዎስ ለየት ያለ ነበር።

ወደ ቲቶ የተጻፈው *መልእክት* ወደ ጢሞቴዎስ ከተጻፈው ከመጀመሪያው *መልእክት* ጋር ተመሳሳይነት ያለው ሲሆን፣ ጳውሎስ በዚህ *መልእክቱ* ስለ ቤተክርስቲያን *መሪዎች* አመራረጥ *መመሪያ* በመስጠት (1:5-9)፣ የሐሰት አስተማሪዎችን ስለ *መገሰጽ* ይናገራል (1:11፣13፣ 3:10)። በመጨረሻም ለቲቶ የግል ተግባጾች ያቀርባል (2:7-8፣15)።

ወደ ቲቶ የተጻፈው መልእክት በተለይ ጎላ አድርጎ የሚያቀርበው በቤተክርስቲያን ጤነኛና ትክክለኛ የሆነ ትምህርትን (sound doctrine) ስለማቅረብ ነው። ጤናማ ወይም ትክክለኛ ትምህርት የሚለው ቃል ሐሰተኛ አስተማሪዎች እንደሚያቀርቡት የተሳሳተና ጤናማ ያልሆነ ትምህርት (unsound doctrine) ሳይሆን፣ ስለ ክርስቶስ እውነቱንና ትክክለኛ የሆነውን ትምህርት ማቅረብ አስፈላጊ እንደሆነ የሚያመልክት ነው።

(6). ለሚከተሉት ጥያቄዎች በማስታወሻ ደብተርህ ላይ አጭር መልስ ጻፍ

ሀ. በቲቶ 1:9 ላይ በተጻፈው *መሠረት* እንድ የቤተክርስቲያን ሽማግሌ ወይም *መሪ* ምን ማድረግ መቻል አለበት?
ለ. በቲቶ 2:1 ላይ በተጻፈው *መሠረት* ቲቶ ማስተማር የነበረበት ምን ነበር?

የሚከተለውን አከፋፈል *መመሪያ* በማድረግ ወደ ቲቶ የተጻፈውን መልእክት እንብብ።

የቲቶ መልእክት፡ ለቤተክርስቲያን መሪ የተሰጠ መመሪያ

I. መግቢያ	1:1-4 አንብብ
II. ሽማግሌዎችን መሾም	1:5-16 አንብብ
III. ምእመናንን ማስተማር	2:1-3:8 አንብብ
IV. መከፋፈል ለሚፈጥሩ የሚወሰድ እርምጃ	3:9-11 አንብብ
V. የመጨረሻ ምክር	3:12-15 አንብብ

ወደ ቲቶ የተጻፈው መልእክት አጭር ቢሆንም፣ ለቤተክርስቲያን ጠቃሚ የሆኑ መመሪያዎችን ያዘለ ነው። በመልእክቱ ውስጥ የሰፈሩት መመሪያዎችና ምክሮች በጣም ጠቃሚ ከመሆናቸውም በላይ፣ የክርስቶስን ቤተክርስቲያን ስማነጽ ስሚፈልጉ አገልጋዮች ሁሉ ጠንካራ መሠረት የሚሆኑ ናቸው።

(7). በቲቶ 2:11-14 ና 3:4-7 ላይ የተጻፈውን ካነበብክ በኋላ የሚከተሉት መግለጫዎች የጎደላቸውን እያሟላህ በማስታወሻ ደብተርህ ላይ አስፍር።

ሀ. 2:13 የተባረከው ተስፋችን_____ ነው።
ለ. 2:14 ኢየሱስ _____ስለ እኛ ነፍሱን ሰጥቷል።
ሐ. 3:5 እግዚአብሔር እንደ _____ መጠን አዳነን።
መ. 3:5 እግዚአብሔር ያዳነን_____ነው።
ሠ. 3:7 የጸደቅነው _____ ነው።
ረ. 3:7 የተሰጠን ተስፋ _____ነው።

ጳውሎስ ወደ ጢሞቴዎስ የጻፈው የመጀመሪያው መልእክትና ወደ ቲቶ የጻፈው መልእክት እንደዚሁም የመጀመሪያው የጴጥሮስ መልእክት የሚያመለክቱት አማኞች ተደራጅተው መሥራትን በይበልጥ ያዳበሩ መሆናቸውን ነው። እንደ ሽማግሌዎችና ዲያቆናት ያሉት የቤተክርስቲያን መሪዎችና አገልጋዮች ከሌሎቹ መልእክቶች ይልቅ በይበልጥ ተጠቅሰው የምናገኘው በእነዚህ መልእክቶች ውስጥ ሲሆን፣ የብቁነት መመዘኛቸውም በሚገባ ተገልጿል።

(8). ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ጥቅሶች ካነበብክ በኋላ ከአንድ የቤተ ክርስቲያን መሪ የሚጠበቀውን በማስታወሻ ደብተርህ ላይ አስፍር።

ሀ. ከሚሰቱ ጋር ያለው ግንኙነትና የሚሰቱ ባህርያት (1ጢሞ 3:1፣ 11-12፤ ቲቶ 1:6)
ለ. ከልጆቹ ጋር ያለው ግንኙነትና የልጆቹ ጠባይ (1ጢሞ 3:4-5፣ 12፤ ቲቶ 1:6)
ሐ. ስለ ገንዘብ ሊኖረው የሚገባ አመለካከት (1ጢሞ 3:8፤ ቲቶ1:7፤ 1ጴጥ 5:2)
መ. በውጭ ባሉት ዘንድ ያለው ምስክርነት (1ጢሞ 3:7)
ሠ. መንፈሳዊ ብስለቱ (1ጢሞ 3:2-9፤ቲቶ 1:9፤ 1ጴጥ 5:2-3)

ሁለተኛው የጢሞቴዎስ መልእክት

ጳውሎስ ለጢሞቴዎስ የጻፈው 2ኛው መልእክት በደረሰው ወቅት ጢሞቴዎስ በኤፌሶን አልነበረም (2ጢሞ 4:12)። ጢሞቴዎስ በዚያን ወቅት በመቄዶንያ ወይም በእስያ በወንጌል አገልግሎት ላይ ሊሆን ይችላል። የጳውሎስም ሁኔታ ተለውጦ እንደገና ወደ እስር ቤት ገብቶ እንደነበር በ2ጢሞ 1:8፣ 2:9 ላይ የተጻፈው ቃል ይነግረናል።

የጳውሎስ ደጋግሞ ወደ ፍርድ ቤት መቅረብና መታሰር የሚያመለክተው የሮም መንግሥት በክርስትና ሃይማኖት ላይ የነበረውን ዝንባሌና አስተያየት ቀስ በቀስ እየቀየረ መሄዱን ነው። በመጀመሪያ የሮም ባለሥልጣኖች ስለ ክርስትና ሃይማኖት ግድ እንዳልነበራቸው በሐዋ 18:14-17 ላይ ከተጻፈው ለመረዳት እንችላለን።

በኋላም አይቶ እንዳላየ ነገሮችን በጥርጥር ማለፍ ጀመሩ (የሐዋ 26:30-32)። ይህ ጥርጥር ቀስ በቀስ ተቃዋሚ ወደ መሆን ተለውጦ በንጉሥ ኔሮ ዘመን በ64 ዓ.ም ብዙ ክርስቲያኖች ስለ እምነታቸው መከራ መቀበላቸውን ታሪክ ያነግረናል። በዚያን ወቅት ስለ እምነታቸው መከራ ከተቀበሉት አንዱ፣ ሞትን ለመቅመስ ዝግጁ እንደነበር ለጢሞቴዎስ በጻፈው መልእክት የተናገረው ሐዋርያው ጳውሎስ ይገኝበታል (2ጢሞ 4:6)።

ወደ ጢሞቴዎስ የተጻፈው ሁለተኛው መልእክት ምክርን፣ ማስጠንቀቂያን፣ ጥብቅ ማሳሰቢያን፣ ልመናንና የግል ትዝታን በጠቅላላው የተለያዩ ነገሮችን በውስጡ ያዘለ ነው። አንድ ሥፍራውን በማስረከብ ላይ ያለ አንጋፋ አገልጋይ ቦታውን ለሚተካ ለታዳጊ አገልጋይ አስፈላጊውን ምክርና አደራ እንደሚሰጥ፣ ጳውሎስም ለጢሞቴዎስ አስፈላጊውን ምክር በመስጠት፣ ታማኝ እንዲሆን ያበረታታዋል (2ጢሞ 1:1-4)። ትጉ ሠራተኛ እንዲሆን ያስገነዝበዋል (2ጢሞ 2:14-26)፤ እየቀረበ ስለሚመጣው ክፉና አስጨናቂ ዘመን ይነግረዋል (3:1-9)፤ የአገልግሎቱንም ተግባሮች በሙሉ እንዲፈጽም አደራ ይለዋል (3:10-4:8)። ከሉቃስ በስተቀር ብቻውን እንደነበረ በመግለጽ፥ "እንደሚወደው ልጁ" የሚቆጥረው ጢሞቴዎስን ቶሎ ወደ እርሱ እንዲመጣለት እያሳሰበ፣ በጢሮአዳ የተወውን ካባና መጻሕፍቱን ይዞለት እንዲመጣ አደራ ይለዋል (4:9-22)።

ከዚህ የሚከተለውን አከፋፈል መመሪያ በማድረግ ወደ ጢሞቴዎስ የተላከውን ሁለተኛውን መልእክት አንብብ።

2ጢሞቴዎስ፡ ለተተኪ አገልጋይ የተሰጠ ተልዕኮ

I. ሠላምታ	1:1-2 አንብብ
II. ለጥሪህ ታማኝ ሁን	1:3-2:13 አንብብ
III. በሥራህ ትጉህ ሁን	2:14-26 አንብብ
IV. ስለ ወደፊቱ ዝግጁ ሁን	3:1-9 አንብብ

V. በቅዱሳት መጻሕፍት ተደገፍ 3:10-17 እንብብ
VI. አገልግሎትህን ፈጽም 4:1-8 እንብብ
VII. የግል ጥያቄዎች 4:9-22 እንብብ

(9). በሁለተኛ ጢሞቴዎስ የሚገኙትን የሚከተሉትን ጥቅሶች ካነበብክ በኋላ ለጢሞቴዎስ የተነገረውን ትዕዛዝ በባዶው ቦታ ጻፍ። ለምሳሌነት የመጀመሪያው ጥያቄ ተሠርቷል።

ሀ. 1:14 የተሰጠህን መልካም እደራ ጠብቅ።
ለ. 2:3 _____ በትዕግሥት ተቀበል።
ሐ. 2:8 - _____ _____እስታውስ።
መ. 3:14 _____ _____ ጽና።
ሠ. 4:2 _____ _____ ስበክ።

(10). የመጋቢነት መልእክቶች የተባሉትን በማጥናት ጳውሎስ አብረው ለሚያገለግሉት ስለ ቤተ ክርስቲያን እድገት ከሰጠው ምክር የምንረዳው

ሀ. ስቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎች የተሰጠውን የብቃት መስፈርት ወይም መለኪያ የሚያሟሉትን እንዲሾሙ መንገር ነበር።
ለ. ስመሪነት ተስማሚ የሆኑትን ስዎች እርሱ መጥቶ እስኪሾም ድረስ እንዲጠብቁ መንገር ነበር።

ሰባኛው የተሰጠ ምላሽ
የመጀመሪያው የጴጥሮስ መልእክት

ዓላማ 2 ስለ መልእክቱ ጸሐፊ፣ስለ መልእክቱ ታሪካዊ መነሻና ይዘት ለመግለጽ።

የመጀመሪያው የጴጥሮስ መልእክት በስደት ላይ ለነበሩ ክርስቲያኖች የተጻፈ ነበር። ከጳውሎስ የመጀመሪያ የሮም እስር ቀጥሎ በነበሩት ዓመታት ስደቱ እየከፋ መሄድ ጀመረ። በተለያዩ ፈተናዎችና መከራዎች ስሚያልፉ አማኞች፣ የክርስቲያኖች እመለካከታቸው ምን መሆን እንዳለበት እስፈላጊውን ምክር ለመስጠት ነበር ጴጥሮስ መልእክቱን የጻፈው።

የመልእክቱ ጸሐፊ

የሐዋርያት ሥራን መጽሐፍ ባጠናንበት ወቅት እንደተመለከትነው ጴጥሮስ የታወቀ የቤተክርስቲያን መሪና ለኢየሱስ ቅርበት ከነበራቸው ክሦስቱ ደቀ መዛሙርት አንዱ እንደነበር በማቴ 26:37 እና በሉቃ 9:26 ላይ የተጻፈው ቃል ያመለክታል። ኢየሱስን በምድራዊ ሕይወቱ በተከተለበት ዘመን ታላቅ መገለጥ እንደነበረው ያስመሰክረ ሲሆን (ማቴ 16:21-23)፣ በሌላ ጊዜ

ደግሞ ክፉ እወዳደቅ እንደወደቀ እንመለክታለን (ማቴ 26:69-75)። ኢየሱስ እንደተነበየው ክወላዋይነት ወደ ጽኑ ሐዋርያነት እንደተለወጠ በማቴ 16:18 እና በሉቃ 22:31-32 የተጻፈው ቃል ይነግረናል። ጴጥሮስ የኢየሱስ ክርስቶስ ብርቱ ተክታይና የወንጌል ስባኪ እንዲሁም የቤተክርስቲያን መሪ እንደነበር ለመገንዘብ ችለናል።

ጴጥሮስ እንደ ሐዋርያው ጳውሎስ ለወንጌል አገልግሎት በየስፍራውና በየአገሩ የተጓዘ መሆኑን በ1ቆሮ 9:5 ላይ የተጻፈው ቃል ሲገልጽ፡- "እንደ ሌሎቹ ሐዋርያትና እንደ ጌታ ወንድሞች፣ እንደ ኬፋም ሚስታችንን ይዘን ለመዞር መብት የለንምን?" በማለት ሐዋርያው ጳውሎስ ይጠይቃል። ጴጥሮስ የሞተውም የሮም ንጉሥ የነበረው ኔሮ በዘመኑ ክርስቲያኖችን ማሳደድ ከጀመረ በኋላ፣ እንደ ሐዋርያው ጳውሎስ የስማዕት ሞት ሳይሆን አይቀርም።

የመልእክቱ መነሻ

ጴጥሮስ የመጀመሪያ መልእክቱን የጻፈው በስደትና በመከራ ላይ ለነበሩና በእስያ ለተበተኑ አማኞች እንደሆነ ክመልእክቱ ለመረዳት እንችላለን (1ጴጥ 1:1፣6፤ 3:14፤ 4:12-19)። ጴጥሮስ መልእክቱን ስጻፈበት ወቅት ለእንባቢዎቹ ማርቆስም ስላምታ ያቀርብላችኋል ስለሚል፣ ቀደም ሲል እካባቢውን ማርቆስ ጎብኝቶት እንደነበር የሚያመለክት ነው (1ጴጥ 5:13)። ይህም የሚያስረዳን መልእክቱ የተጻፈው ከመጀመሪያው የጳውሎስ የሮም እሰራት በኋላ እንደሆነ ሲሆን፣ በዚያ ወቅት ማርቆስ እካባቢውን ለመጎብኘት እቅዶ ገና እንዳልነበኘ በቆላ 4:10 ላይ የተጻፈው ቃል ይነግረናል።

መልእክቱን የጻፈላቸውን አማኞች ስግል ተገናኝቶ ባይተዋወቃቸውም፣ እነዚህ አማኞች የገጠማቸውን ችግሮች ግን በሚገባ ሊረዳ የቻለው ክማርቆስ ሊሆን ይችላል። እነዚህ አማኞች በመጀመሪያ ወንጌልን እንዴት እንደስሙ የሚገልጽ ማስረጃ የለም። ሆኖም ግን ወደ ጌታ የመጡት ጳውሎስ በኤፌሶን ያገለግል በነበረበት ወቅት እንደሚሆን ይገመታል (የሐዋ 19:10)። ጴጥሮስ በመልእክቱ ላይ በመካከላቸው የነበሩትን "የቤተክርስቲያን ሽማግሌዎች" መጥቀሱ እንደ አብያተ ክርስቲያናት መደራጀታቸውን ያሚገልጽ ማበረጃ ነው (1ጴጥ 5:1)። ሌሎችም መክሬ እየተቀበሉ መሆኑን ብመልእክቱ ላይ ስለሚገልጽ፣ መክራቸውና ስቃያቸው ንጉሥ ኔሮ ካስነሳው ስደት ጋር የተያየዘ ሊሆን እንደሚችል የሚያመለክት ነው (1ጴጥ 5:9)።

ጴጥሮስ እነዚህን አማኞች የሚያበረታታቸው የሚያሳድጷቸውን ብክርስቲያናዊ መንፈስ እንዲመለክቷቸው ነው (1ጴጥ 2:20-23)። ጊዜያዊ ያሆነውን የምድራዊ ስቃይ ዘላለማዊ ከሆነው ስማያዊ ክብር ጋር ብማነጻጸር (1:6-7፤5:10)፣ በመክራቸው ውስጥ ሊኖራቸው የሚችለውን ተስፋ ይገልጻል (1:1-12)። በስ መንፈሳዊ ጥሪያቸው አማኞቹን በማሳሰብ (1:13-2:3)፣ የእግዚአብሔር ልጆች በመሆናቸው የተሰጣቸውን የክብር ስፍራ ይገልጻል (2:4-12)። ከባለሥልጣኖች ጋርና እርስ በርሳቸው ሊኖራቸው

ስለሚገባ ግንኙነት ተገቢውን መመሪያዎች በመሰጠት (2፡13-3፡7)፣ ትክክል የሆነውን ማድረጋቸውን እንዲቀጥሉ ያበረታታቸዋል (3፡8-22)። ስለ ክርስቶስ ስቃይ አሳልፈው በሚሰጡበት ወቅት ሊኖራቸው በሰሚገባ ክርስቲያናዊ አስተያየት እሰረሳጊውን ገለጻ በማድረግ (4፡1-19)፣ ለሽማግሌዎችና ሰወጣቶች ተገቢውን ምክር በመስጠት ሁሉም በእግዚአብሔር ጹጋ ጸንተው እንዲቆሙ ያሳስባል (5፡1-14)።

1ጴጥሮስ፡ ስለ መከራ የተሰጠ ምክር

የሚከተለውን አከፋፈል እንደ መመሪያ በመጠቀም የመጀመሪያውን የጴጥሮስን መልእክት አንብብ፡-

I. ሕያው ተሰፋችን	1፡1-12 አንብብ
II. በክቡር ደሙ መዋጀታችን	1፡13-2፡3 አንብብ
III. የክብር ሰፍራችን	2፡4-12 አንብብ
IV. የግል እርእያነታችን	2፡13-25 አንብብ
V. ውጫዊ አካሄዳችን	3፡1-22 አንብብ
VI. ውሰጣዊ ዝንባሌያችን	4፡1-19 አንብብ
VII. ዘላለማዊ ክብራችን	5፡1-14 አንብብ

(11). የመጀመሪያው የጴጥሮስ መልእክት፡-

ሀ. እማኞች ሰው ለሾማቸው ባለ ሥልጣኖች መታዘዝ እንደሚያሰፈልጋቸው ይናገራል።
ለ. በመቄዶንያ ለሚኖሩ እማኞች የተጻፈ ነበር።
ሐ. ሽማግሌዎች ማሟላት የሚገባቸውን መመዘኛዎች ይዘረዝራል።
መ. በመከራ ጊዜ ለመከተል ክርስቶስን ምሳሌ አድርን ያቀርባል።
ሠ. ምናልባት የተጻፈው ከጳውሎስ የመጀመሪያ የሮም እሰራት በኋላ ሳይሆን አይቀርም።
ረ. የቤተክርስቲያን መሪዎች እንዲከተሉት የሰጠው ምንም መመሪያ የለም።

የጥንቶቹ እማኞች የመጀመሪያውን የጴጥሮስን መልእክት ሊያነቡ መልእክቱ ትልቅ መበረታታትንና መጽናናትን እንደሰጣቸው የማይጠረጠር ነው። በመልእክቱ ጸሐፊ በሐዋርያው ጴጥሮስ ሕይወት ውሰጥ የእግዚአብሔር ኃይል ምን ያህል አበገራሚ እንደሆነ የሚያሰረዳና ታላቅ ምስክርነት እንደሆነ የሚያሳየው በአንድ ወቅት ጌታን ክዶ የነበረው ጴጥሮስ በመልእክቱ ወንድሞቹን የሚያጽናና የሚያበረታታ መሆኑ ነው (ሉቃ 22፡32)። እኛም ዛሬ ጴጥሮስ መንፈስ ቅዱስ መርቶት የጻፈው የመጀመሪያውን መልእክቱን በማንበብ መንፈሳዊ ብርታትንና መጽናናትን እናገኛለን።

ስለአይሁድ ሃይማኖት የተሰጠ ምላሽ፡ ወደ ዕብራውያን የተጻፈ መልእክት

ዓላማ 3 ወደ ዕብራውያን የተጻፈውን መልእክት ታሪካዊ መነሻና የሚለጠውን ትምህርት ለመግለጽ።

ወደ ዕብራውያን በዎች የተጻፈው መልእክት ክርስቶስ ከሁሉ በላይ መሆኑን የሚያበረዳ ሲሆን፣ ብዙ የአይሁድ ክርስቲያኖች የብሉይ ኪዳን ሕግ ከክርስቶስ ሥራ ጋር እንዴት ሊዛመድ እንደሚችል አሰቸጋሪ ሆኖ እንዳገኙት ቀደም ሲል በሐዋርያት ሥራና በገላትያ መጽሐፎች ላይ ካደረግነው ጥናት ለመረዳት ችለናል። የአይሁድ ሃይማኖት ተከታዮች ግዝረት ላይ በማተኮር ሲከራከሩ፣ ሐዋርያው ጳውሎስ ደግሞ እውነተኛው ወንጌል ላይ በማተኮር እነርሱን መቃወም ነበረበት። ሌሎች የአይሁድ ክርስቲያኖች ደግሞ እምነታቸውን ሙሉ በሙሉ በእርሱ ላይ በመጣል ፋንታ በአይሁድ መቅደስና ከመቅደሱ ጋር ከተያያዙ ሥርዓቶች ጋር ተጣብቀው በለ ነበር ከዚህ መሳቀቅ ነበረባቸው። የዕብራውያን ጸሐፊ መልእክቱን ያዘጋጀው እንደነዚህ ዓይነቶቹን ለመርዳት ነበር።

የመልእክቱ ጸሐፊ

መልእክቱን የጻፈው ሰው ሰም በመልዕክቱ ውሰጥ ሰሳልተጠቀሰ፣ ማን እንደጸፈውም የሚገልጽ ተጨባጭ ማሰረጃ ባለመኖሩ፣ ጸሐፊው ማን እንደሆነ በትክክል አይታወቅም። የመጽሐፍ ቅዱስ ሊቃውንት ጳውሎሰ ወይም አጵሎሰ ወይም በርናባስ ሊሆኑ እንደሚችሉ ሃሳብ ቢያቀርቡም፣ የመልእክቱ አጻጻፍ ግን መልእክቱን የጻፈው ከእነዚህ እንዱ መሆኑን በእርግጠኛነት እያመለክትም። የሚታወቅ ነገር ቢኖር ጸሐፊው የመልእክቱን ተቀባዮች ለመንቦኘት መፈለጉና ጢሞቴዎሰን የሚያውቅ ሰው መሆኑ ብቻ ነው (ዕብ 13፡19፣23)። ከመጀመሪያዎቹ ደቀ መዛሙርት እንዱ ባይመሰልም (2፡3)፣ መልእክቱ የሚሰጠው ትምህርት ግን ሐዋርያት ከሰጡት ትምህርት ጋር ሙሉ በሙሉ የሚስማማና ከመጀመሪያው እስከ መጨረሻው ስህተት የሌለበት መለኮታዊ እመራርን የተከተለ ነው።

መልእክቱ እንደሚያመለክተው የተጻፈው ሰአይሁድ ክርስቲያኖች ነሆንም፣ በመልእክቱ ውሰጥ የቦታ ወይም የከተማ ሰም ሰሳልተጠቀሰ መልእክቱ የተጻፈላቸው ክርስቲያኖች የት ይኖሩ እንደነበር አይታወቅም። ይመሰላሉ ተብለው የታሰቡት ሁለቱ ስፍራዎች ሮምና ኢየሩሳሌም ናቸው (ዕብ 13፡24)። መልእክቱ የተጻፈው በ60ዎቹ ዓ.ም መጨረሻ ገደማ ከኢየሩሳሌምና ከመቅደሱ መፈራረስ በፊት (በ70 ዓ.ም) ሳይሆን አይቀርም።

(12). በዕብራውያን 2፡3-4፣ 10፡32-34 ላይ በተጻፈው መሠረት፣ መልእክቱ የተጻፈላቸው ክርስቲያኖች

ሀ. ወንጌልን በመጀመሪያ የተቀበሉት በቀጥታ ከጌታ ከሰሙት ሐዋርያት ነበር።
ለ. ስደት ለመጀመሪያ ጊዜ ያጋጠማቸው አዲስ ክርስቲያኖች ነበሩ።
ሐ. በእምነታቸው ምክንያት መከራ የተቀበሉ ክርስቲያኖችም ነበሩ።

የመልእክቱ ይዘት

የዕብራውያን አሐፊ መልእክቱን የጻፈላቸው ሰዎች በእምነት ጸንተው ራሳቸውን ሙሉ በሙሉ ለክርስቶስ ከመስጠት ይልቅ ወደ ኋላ ማፈግፈግ መጀመራቸውን ተረዳ። እግዚአብሔር በልጁ በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ለገለጠላቸው እውነት ከመታዘዝ ይልቅ ለመቅደሱና በዚያ ስሚካሄዱት ሥርዓቶች ለመታዘዝ ማዘንበል ጀምረዋል። የመልእክቱ አሐፊ ለእነዚህ ሰዎች የጻፈው የነበሩበትን እደገኛ ሁኔታ ለማሳየትና ክርስቶስ ክሁሉ በላይ መሆኑን በመግለጽ የፈጸማቸው ሥራዎች ከሃይማኖታዊ ደንቦችና ሥርዓቶች በላይ መሆኑን ለማሳየት ነበር።

ይህንንም ያደረገው ክርስቶስ እንዴት ከመላእክት (1፡-2፡18)፣ ከሙሴ (3፡1-4፡13) ከአሮንም በላይ እንደሆነ በመልእክቱ በመግለጥ ነው (4፡14-7፡28)። በመቀጠልም አዲሱ ስምምነት (ኪዳን) ከአሮጌው ይልቅ እንዴት የተሻለ እንደሆነ በመግለጥ (8፡1-9፡28)፣ ጋጢአትን ሊያስወግድ የቻለ የክርስቶስ መሥዋዕትነት ብቻ እንደሆነ ያብራራል (10፡1-31)። ከዚያም የእምነትን አስፈላጊነት በመጥቀስና (10፡32-12፡29) መልእክቱ በተግባር ላይ የሚውልበትን መንገዶች በማመልከት መልእክቱን ያጠቃልላል (13፡1-25)። በመልእክቱም ውስጥ ቧርከት ያሉ ማስጠንቀቂያዎችና ማሳሰቢያዎች ተቀናብረው ይገኛሉ (2፡1-4፣ 4፡18፣ 12፡1)።

ዕብራውያን፡ ክርስቶስ ከሁሉ የሚበልጠው፡-

I. *ስሙ ከፍ ያለ ነው።*	1፡5-2፡18 እንብብ
- ከመላእክት ጋር ሲነጻጸር	
II. *ሥልጣኑ ከፍ ያለ ነው።*	3፡1-4፡13 እንብብ
- ከሙሴና ከኢያሱ ጋር ሲነጻጸር	
III. *ክህነቱ ዘላለማዊ ነው።*	4፡14-7፡28 እንብብ
- ከአሮንና ከመልከጼዴቅ ጋር ሲነጻጸር	
IV. *ኪዳኑ ዘላለማዊ ነው።*	8፡1-9፡28 እንብብ
- ከአሮጌው ኪዳን ጋር ሲነጻጸር	
V. *መሥዋዕቱ የመጨረሻ ነው።*	10፡1-31 እንብብ
- በየዓመቱ ከሚቀርበው ጋር ሲነጻጸር	
VI. *ተስፋው እሙን ነው።*	10፡32-12፡13 እንብብ
- የእምነት አርበኞች ምሳሌዎች	
VII. *መንግሥቱ የማይናወጥ ነው።*	12፡14-13፡25 እንብብ
- ከክርስቶስ ጋር የመተባበር ምክር	

(13). ከዚህ የሚከተሉት በዕብራውያን መልእክት ውስጥ የሚገኙ ለድስት ማስጠንቀቂያዎች ሲሆኑ፣ በተሰጠው ባዶ ስፍራ ቁጥሩን በማስቀመጥ እብሮ የሚሄደውን እመልክት።

1. 2፡1-4	4. 5፡11-6፡12
2. 3፡7-19	5. 10፡19-31
3. 4፡11-13	6. 12፡25-29

_____ሀ. ባለማመን ምክንያት ከእግዚአብሔር አትራቅ።
_____ለ. የእግዚአብሔርን ልጅ እምቢ አትበል።
_____ሐ. ክሰማይ የሚናገረውን አትቃወም።
_____መ. በክርስቶስ የሚገኘውን ድነት ችላ አትበል።
_____ሠ. እመጸኛና የማትታዘዝ አትሁን።
_____ረ. ሀጻን ሆነህ እትቅር።

(14). የክርስቶስን ክህነትና የሌዊን ክህነት በማነጻጸር ከዕብራውያን መልእክት የተወሰዱ እራት ምንባቦች ተዘርዝረዋል። በተሰጠው ምንባብ መሠረት ተመሳሳይነቱን ወይም ልዩነቱን በማስፈር እያንዳንዱን ዐረፍተ ነገር የተሟላ አድርግ።

ሀ. አሮን ካህን እንዲሆን በእግዚአብሔር ተጠርቶ ነበር (5፡4-6)።
ክርስቶስ _____
ለ. የብሉይ ኪዳን (ሌዋውያን) ካህናት ሁሉም ስለሞቱ ያገለግሉት በጊዜያ ዊነት ነበር (7፡23-25)። ክርስቶስ የሚያገለግለው _____
ሐ. የብሉይ ኪዳን (ሌዋውያን) ካህናት በሰው እጅ ወደ ተሰራው የማደሪያው ድንኳን የገቡት የእንስሳት ደም ይዘው ነበር (9፡11-14)። ክርስቶስ የገባው _____
መ. የብሉይ ኪዳን (ሌዋውያን) ካህናት በየዓመቱ መሥዋዕት ያቀርቡ ነበር (9፡23-28)። ክርስቶስ ያቀረበው _____

ቀደም ሲል እንደተመለከትነው የዕብራውያን መልእክት ስለ ክርስቶስና ስለ አከናወናቸው ሥራዎች ጠለቅ ያሉ እውነቶችን ያዘለ ነው። መልእክቱ ለተጻፈላቸው ለአይሁድ ክርስቲያኖች አስፈላጊ የሆነውን ያህል ዛሬም ለእኛ አስፈላጊያችን ነው። እኛም እንደ እነርሱ ዓይናችንን ሲቀ ካህናችን ክርስቶስ ላይ አድርገን የእምነት ሩጫችንን መፈጸም እሰብን (ዕብ 12፡1-2)። በዚች ስዓት እንኳ እርሱ ስለኛ ሳያቋርጥ በአባቱ ዘንድ በመማለድ ላይ መሆኑን ማወቅ ራሱ ደስ የሚያሰኝ ተስፋ ነው (ዕብ 7፡25)።

የመከራ ፈተና

1. አዛምድ፡- በክፍሉ ስፍራ ቁጥሩን በማስፈር ከመጽሐፉ ርዕስ፣ ከታሪካዊ መነሻውና ከይዘቱ ጋር አብሮ የሚሄደውን አመልክት።

1. 1ኛ ጢሞቴዎስ	4. 1ኛ ጴጥሮስ
2. 2ኛ ጢሞቴዎስ	5. ዕብራውያን
3. ቲቶ	

___ሀ. "ለተተኪ አገልጋይ የተሰጠ ተልዕኮ" የሚል ርዕስ ያለው።
___ለ. "ስለ መከራ የተሰጠ ምክር" የሚል ርዕስ ያለው።
___ሐ. ስለክርስትና እምነትና በአይሁድ ሃይማኖት መካከል ያለውን ግንኙነት የሚገልጽ።
___መ. ጳውሎስ ጉዞውን ሲቀጥል በኤፌሶን ተባባሪው ለነበረ የተጻፈ።
___ሠ. "ክርስቶስ ከሁሉ የሚበልጠው" የሚል ርዕስ ያለው።
___ረ. "ለእግዚአብሔር ስው የተሰጠ መመሪያ" የሚል ርዕስ ያለው።
___ሰ. በቀርጤስ ደሴት አማኞችን ያደራጅ ለነበረ ስው የተጻፈ።
___ሸ. በአስያ በስደት ምክንያት ይስታቀዩ ለነበሩ አማኞች የተላከ።
___ቀ. "ለቤተክርስቲያን መሪዎች የተሰጠ መመሪያ" የሚል ርዕስ ያለው።
___በ. የክርስቶስን ሥራ ቸል ስለማለት ብዙ ማስጠንቀቂያዎችን የያዘ።
___ተ. ጳውሎስ እንደገና በሮም ታስሮ በነበረ ጊዜ የጻፈ።

ምርጫ፡- ትክክለኛውን መልስ ምረጥ

2. የትክክለኛና የጤናማ ትምህርት (sound doctrine) አስፈላጊነት በተለይ ጎላ ብሎ የተጠቀሰው
   ሀ. በቲቶ ለ. በ1ኛ የጴጥሮስ ሐ. ስዕብራውያን

3. ወደ ዕብራውያን በተጻፈው መልእክት መሠረት የክርስቶስ ክህነት በይበልጥ ተመሳሳይነት ያለው
   ሀ. ከሌዊ ካህናት ለ. ከአሮን ሐ. ክመልከ ጼዴቅ

4. ጳውሎስ ለተባባሪዎቹ አገልጋዮች የጻፋቸው መልእክቶች እንደሚያመለክቱት የቤተክርስቲያን መሪዎችን ሲመርጡ ቅድሚያ ሊሰጠው የሚገባው
ሀ. የንግግር ችሎታቸው
ለ. መሪዎች ሆነው ስቤተክርስቲያን ለማገልገል ያላቸው ፍላጎት
ሐ. የመንፈሳዊ ብስለታቸውና የቤተሰብ ማስተዳደር ችሎታቸው

5. በመጀመሪያው የጴጥሮስ መልእክት ላይ ከተጠቀሱት ዋና ትምህርቶች እንደኛው፡- ሀ. ትክክለኛ የሆነ መሠረታዊ ትምህርት ማስተማር
   ለ. በመከራ ውስጥ ክርስቶስን መምሰል
   ሐ. ለመሪነት ሥፍራ የእግዚአብሔር ስዎችን መምረጥ

6. አጭር መልስ፡- የሚከተሉት ጥቅሶች በዚህ ክፍለ ትምህርት ውስጥ ከጠናናቸው ከአምስቱ መልእክቶች ውስጥ የተውጣጡ ናቸው። ከየትኛው መልእክት እንደተወሰዱ የመጽሐፉን ወይም የመልእክቱን ስም ጻፍ።

ሀ. እንተ ግን ሕይወት ለሚገኝበት ትምህርት የሚገባውን ተናገር፤ . . . ስዎችን ሁሉ የሚያድን የእግዚአብሔር ጸጋ ተገልጦአልና።
ለ. ቃሉን ስበክ . . . ጽና፣ መልካሙን ገድል ተጋድዬአለሁ . . . ቶሎ ወደ እኔ እንድትመጣ ትጋ።
ሐ. እርሱ ግን ስለ ኃጢአት አንድን መሥዋዕት ለዘላለም እቅርቦ ስእግዚእ ብሔር ቀኝ ተቀመጠ።
መ. ክርስቲያን በመሆን ግን መከራን ቢቀበል ስለዚህ ስም እግዚአብሔርን ያመስግን እንጂ እይፍራ።
ሠ. አንዳንዶች ልዩ ትምህርትን እንዳያስተምሩ አንድታዝ በኤፌሶን ተቀመጥ።
ረ. እንዲህ ያለውን ታላቅ መዳን ቸል ብንለው እንዴት እናመልጣለን

የጥናት ማጠናከሪያ ጥያቄ መልሶች

8. መልሶችህ ከዚህ በታች ከተሰጡት ጋር ተመሳሳይ መሆን አለባቸው።

ሀ. በጠባይዋ የተመሰገነች አንዲት ሚስት ሊኖረው ይገባል።
ለ. ልጆቹን ማስተዳደር መቻል አለበት። እነርሱም እርሱን የሚያከብሩና መልካም ጠባይ ያላቸው፣ አማኞች መሆን አለባቸው።
ሐ. ትክክል ባልሆነ መንገድ ገንዘብ እትራፊ ወይም ገንዘብ እፍቃሪ መሆን የለበትም።
መ. በውጭ ባሉት ስዎች ዘንድ መልካም ምስክርነት ሊኖረው ይገባል።
ሠ. ሌሎችን ማስተማር፣ ማበረታታት፣ እንዲሁም በእውነት መኖር መቻል አለበት። አዲስ አማኝ መሆን የለበትም።

1. ሀ. መቄዶንያ
   ለ. ቀርጤስ
   ሐ. ኒቆጵልዮን
   መ. ቆሮንቶስና ሚልጢን
   ሠ. ጢሮአዳ

9. መልሶችህ ከዚህ በታች ከተሰጡ ጋር ተመሳሳይ መሆን አለባቸው።
   1:14 ምሳሌውን ተመልከት።
   2:3 መልካም ወታደር በመሆን መከራን።
   2:8 ኢየሱስ ክርስቶስን።
   3:14 በተማርከው እውነት።
   4:2 ቃሉን።
2. ሐ

10. ሀ

3. ሀ. 2 ሐ. 1 ሠ. 2
ለ. 1 መ. 1

11. ሀ
መ
ሠ

4. ለ

12. ሀ እና ሐ

5. መልሶችህ ከዚህ በታች ከተሰጡት ጋር ተመሳሳይ መሆን አለበት።

ሀ. ጢሞቴዎስ ከገንዘብ ፍቅር መሸሽ ነበረበት።
ለ. የጽድቅ፣ የመንፈሳዊ፣ የእምነት፣ የፍቅር፣ የትዕግሥትና የጨዋነት ሕይወት መከተል።
ሐ. የእምነት ገድል መጋደል ነበረበት።
መ. የዘላለም ሕይወትን እጥብቆ መያዝና የተሰጠውን ትእዛዝ መጠበቅ ነበረበት።

13. ሀ. 2 ሐ. 6 ሠ. 3
ለ. 5 መ. 1 ረ. 4

6. መልሶችህ ከዚህ በታች ከተሰጡት ጋር ተመሳሳይ መሆን አለበት።
ሀ. ትክክለኛ በሆነ ትምህርት (sound doctrine) ሌሎችን ማበረታታት መቻል አለበት።
ለ. ከትክክለኛ ትምህርት (sound doctrine) ጋር የሚስማማውን ማስተማር አለበት።

14. መልሶችህ ከዚህ በታች ከተሰጡት ጋር ተመሳሳይ መሆን አለበት።

ሀ. ክርስቶስ ደግሞ እንደ መልከ ጼዴቅ ሹመት ለክህነት ተጠርቷል።
ለ. ክርስቶስ ለዘላለም ስለሚኖር የሚያገለግለው ለዘለዓለም ነው።
ሐ. ክርስቶስ ወደ ሰማያዊው ቅድስተ ቅዱሳት የገባው በራሱ ደም ነው።
መ. ክርስቶስ ራሱን መሥዋዕት አድርጎ ያቀረበው ለዘላለም ነው።

7. መልሶችህ ከዚህ በታች ከተሰጡት ጋር ተመሳሳይ መሆን አለባቸው።

ሀ. የክርስቶስ በክብር መገለጥ
ለ. ሊቤገሩንና ሊያነጻን
ሐ. ምህረት
መ. ለአዲስ ልደት በሚሆነው መታጠብና በመንፈስ ቅዱስ መታደስ
ሠ. በጸጋ
ረ. የዘላለም ሕይወት

9 የቤተክርስቲያን ተጋድሎና ተስፋ

ትምህርት

በሰባተኛው ክፍለ ትምህርት ላይ የመጋቢነት መልእክቶች የተባሉትንና የመጀመሪያውን የጴጥሮስን እንደዚሁም የዕብራውያንን መልእክቶች እጥንተናል። በዚህ ትምህርት ቤተክርስቲያን እንዴት በአቋም እየተጠናከረች እንደሄደች ተመልክተናል። የበደትና የመከራ ጊዜም ሲኖር የሚገባው ምላሽና አስተያየት እንዴት መሆን እንዳለበት በቂ ግንዛቤ እግኝተናል። በእይሁድ ሃይማኖትና በክርስትና እምነት መካከል በሳለው ግንኙነትም ግልጽ በሆነ መንገድ ለመረዳት ችለናል።

በዚህ በዘጠነኛው ክፍለ ትምህርት የምናጠናቸው ደግሞ ጳውሎስ ከሞተ በኋላ ባሉት ዓመታት የተጻፉትን መልእክቶች ነው። እነዚህ ጊዜያት በብዙ መንገድ ለቤተክርስቲያን በጣም አስቸጋሪና የክርስትናን መሠረታዊ እውነቶችን ለማናጋት የሐሰት መምህራን እየተሰፋፉ የሄዱበት ዓመታት ነበሩ። ስደት እየጠነከረና እየተስፋፉ የሄደባቸው ከባድ የፈተና ዓመታትም ነበሩ።

የእግዚአብሔር መንፈስ ግን እንደገና ለመሪዎች ጥበብና ምሪት በመስጠት፣ ጴጥሮስ፣ ይሁዳና ዮሐንስ በጻፉአቸው መልእክቶች ከሐሰት መምህራን እንዲጠበቁና እንዲጠነቀቁ እደረጉ። ዮሐንስ በጻፈው በራዕይ መጽሐፍም እማኝነት እማኞች በመከራ ውስጥ ቢያልፉም ለክርስቶስ ታማኝ ሆነው እንዲቆዩ ተበረታቱ። የክርስቶስን በክብር መመለስና ፍጹም ድል እድራጊነት የማየት ችሎታ እገኙ።

ይህንን ክፍለ ትምህርት ስታጠና እነዚህን መጻሕፍት ለመረዳት የሚያግዙ ሀ በርካታ ቁም ነገሮችን ትማራለህ። ዛሬም ቢሆን ለእኛ ታላቅ መልዕክት የያዙ እንደሆኑ ትገነዘባለህ። ተመሳሳይ የሆኑ የሀሰት ትምህርቶችና ፈተናዎች የሚገጥሙን በመሆኑ ከመጀመሪያዎቹ እንባቢዎች ይልቅ በራዕይ ውስጥ ለሰፈሩት ትንቢቶች መፈጸም እኛ በጣም የቀረብን ነን።

የክፍለ ትምህርቱ እከፋፈል

- **የቤተክርስቲያን ተጋድሎ በሐሰት ትምህርት ላይ፡**
  ሁለተኛው የጴጥሮስ መልእክት
  የይሁዳ መልእክት
  የዮሐንስ መልእክት 1-3
- **የቤተክርስቲያን ተስፋ የክርስቶስ ዳግም ምጽአት**
  የዮሐንስ ራዕይ መጽሐፍ

የክፍለ ትምህርቱ ዓላማዎች

ይህን ክፍለ ትምህርት ስትጨርስ ከዚህ የሚከተሉትን ማድረግ መቻል አለብህ።

- የሁለተኛ ጴጥሮስን፣ የይሁዳንና የዮሐንስን መልእክቶች 1-3 ይዘት በአጭሩ መግለጽ።
- ጴጥሮስ፣ ይሁዳና ዮሐንስ ምላሽ የሰጡባቸውን የሐሰት ትምህርቶች መግለጽ።
- የዮሐንስ ራዕይን ታሪካዊ መነሻ መግለጽ።
- የዮሐንስ ራዕይ መጽሐፍ የሚተረጎምበትን አራት መንገዶች ለይቶ ማወቅና ትርጉሙን መግለጽ።

የክፍለ ትምህርቱ መመሪያዎች

- እንደተለመደው ትምህርቱን በመከታተል ዋና ነጥቦቹን መያዝ።
- የተሰጠውን መመሪያ በመከተል ሁለተኛ ጴጥሮስን፣ የይሁዳንና የዮሐንስን መልእክቶች 1-3 እንብብ።
- በራዕይ ምዕ2 እና 3 ላይ የተጠቀሱትን የሰባት እብያተ ክርስቲያናት ስም አጥና።
- ትምህርቱን በሚገባ ካጠናህ በኋላ የመጨረሻ ፈተናውን በመውሰድ በትክክል ያልመለስካቸውን እስተካክል።

የትምህርቱ ዝርዝር

በመጀመሪያ የምናጠናው በቀድሞዋ ቤተ ክርስቲያን ሰርጎ የገባውንና የውስጥ ችግር የሆነውን የሐሰት ትምህርት ለመቃወም የተጻፉትን ሲሆን፣ እነዚህም መልእክቶች ሁለተኛ ጴጥሮስ፣ ይሁዳና ዮሐንስ 1-3 ናቸው፤ ከዚያም ስለ ዮሐንስ ራዕይ መጽሐፍ ልዩ ሁኔታዎችና በውስጡ የያዘውን የተስፋና የድል መልእክት እንመለከታለን።

የቤተክርስቲያን ተጋድሎ በሐሰት ትምህርት ላይ፡
ሁለተኛ ጴጥሮስ፣ የይሁዳ መልዕክትና የዮሐንስ መልዕክት 1-3

ዓላማ 1 የሐሰት ትምህርቶችን ለመቃወም የተጻፉትን መልእክቶች መነሻና ይዘት እንደዚሁም የሐሰት ትምህርቶቹ ምን እንደሆኑ ለመግለጽ።

ጳውሎስ ለኤፌሶን ሽማግሌዎችንና ለጢሞቴዎስ እንዲሁም ለቲቶ ሐሰተኛ ሰዎች ተነሥተው እውነት ያልሆኑ ነገሮችን እንደሚያስተምሩ አስቀድሞ ተናግሮ ነበር (ሐዋ 20፡29-30፤ 2ጢሞ 4፡3-4፤ቲቶ 1፡10-11)። በሁለተኛ ጴጥሮስ፣ በይሁዳና በዮሐንስ መልእክቶች 1-3 ላይ ለተነሱት የሐሰት ትምህርቶች ሌሎች የቤተክርስቲያን መሪዎች እንዴት ምላሽ እንደሰጡ እንመለከታለን።

ሁለተኛው የጴጥሮስ መልእክት

ሁለተኛው የጴጥሮስ መልእክት የተጻፈው ከ65-67 ዓ.ም መካከል ሊሆን እንደሚችል ይገመታል። የመልእክቱ ይዘት እንደሚያመለክተው የመጀመሪያውን መልእክቱን ለላከላቸው አማኞች ነበር የጻፈው (2ጴጥ 1፡13፡1)። መልእክቱ ያተኮረው እንደመጀመሪያው የቤተክርስቲያን የውጭ ችግር በሆነው በስደት ላይ ሳይሆን የውስጥ ችግር በነበረው በሐሰተኛ አስተማሪዎች ላይ በመሆኑ የአማኞች ሁኔታ ከበፊቱ ይልቅ የተለወጠ ይመስላል።

ሐዋርያው ጴጥሮስ በመልእክቱ ስለ ክርስቶስ እውነተኛውን ዕውቀት የሐሰት መምህራን ካመጡት የመናፍቃን ትምህርት ጋር በማነጻጸር ልዩነቱን ይገልጻል። በክርስቶስ የሚገኘውን እውቀት ፍጹምነትና መነሻው ከየት እንደሆነ ለእንባቢዎች ይገልጻል (2ጴጥ 1፡1-21)። ከሐሰተኛ መምህራን ክፉ ባሕርይና ጥፋት ከሚያስከትለውም የሐሰት ትምህርታቸው እንዲጠበቁ እንባቢዎቹን ያስጠነቅቃል (2፡1-22)።

ስለ ጌታ ቀን መምጣት እንዳንዶች ስለሚከተሉት ያለማመን ዝንባሌ በመተንበይ (3፡1-7)፣ ለክርስቶስ መምጫ ዝግጁ ለመሆን ክርስቲያናዊ

ኑሮአቸውን በሚገባ እንዲኖሩ በመምከር መልእክቱን ያጠቃልላል (3፡8-18)። የጴጥሮስን መልእክት የተቀበሉ እማኞች በመካከላቸው የተነሱትን የሐሰት መምህራን ስይቶ ማወቅ ብቻ ሳይሆን፣ በሚያቀርቡላቸው የሐሰት ትምህርት እንዳይታለሉም ዝግጁ ያደርጋቸዋል።

ከዚህ በታች የሰፈረውን እከፋፈል መመሪያ በማድረግ የመጀመሪያውን የጴጥሮስን መልእክት እንብብ።

2ኛ ጴጥሮስ፡ የእውነተኛ ክርስቲያን እውቀት

I. የክርስቶስ እውቀትና መሠረቱ	1፡1-21 እንብብ
II. የሐሰት መምህራንና ፍርዳቸው	2፡1-22 እንብብ
III. የጌታ ቀንና ክርስቲያናዊ እኖኗር	3፡1-18 እንብብ

(1). በ2ጴጥ 2፡1-2 ላይ በተጻፈው መሠረት የሐሰት መምህራኑ

ሀ. የሐሰት ትምህርታቸውን በግልጽ ይሰብካሉ።
ለ. ምንም ተከታዮች እሳገኙም።
ሐ. የገዛቸውን ጌታ ይክዳሉ።

(2). የሐሰት መምህራኑ እማኞቹን ለማሳት የፈጠሩትን ተረት እንደሚናገሩ ጴጥሮስ በመልእክቱ ይናገራል (2ጴጥ 2፡3)። ጴጥሮስ ሲናገር ስለ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ኃይልና ስለመምጣቱ የነገርናችሁ የእርሱን ግርማ _____ እንጂ በሰዎች ጥበብ የተፈጠረውን ተረት ተከትለን አይደለም። (2ጴጥ 1፡16)። ከዚያም በመቀጠል በዚሁ ምዕራፍ በቁ. 19 ላይ _____ ተረጋግጦልናል ይላል። በቁ. 21 ላይ ደግሞ ትንቢት ከቶ በሰው ፈቃድ እልመጣም፣ ዳሩ ግን _____ተልከው ቅዱሳን ሰዎች ተናገሩ ይላል።

(3). በ2ጴጥ 3፡1-13 ላይ ስለ ጌታ ቀን በዛ ያሉ መግለጫዎች ሰፍረዋል። በተሰጡት መግለጫዎች መሠረት፦

ሀ. የጌታ ቀን የዘገየው ለዎች ንስሐ እንዲገቡ እግዚአብሔር ጊዜ ሲሰጣቸው ስለፈለገ ነው።
ለ. ስለ ጌታ ቀን ተስፋ ሰዎች የሚዘባበቱት ካለማወቅ የተነሣ ነው።
ሐ. በው ሁሉ የጌታን መመለስ የሚጠባበቅ ይሆናል።

ሁለተኛው የጴጥሮስ መልእክት ከውስጥ ቤተክርስቲያንን ለማፍረስ ለሚሞክር ስማንኛውም ሰው ከበድ ያለ ማስጠንቀቂያ በማቅረብ፣ ለሐሰት መምህራን የፍርድ ቀን በእርግጥ እንደሚመጣ ይገልጻል (2ጴጥ 3፡12-13፡17)። በተጨማሪም እኛ ለጌታ መምጫ ዘወትር ዝግጁዎች በመሆን ያለ ነውርና ያለ ነቀፋ ሆነን በሰላም በእርሱ እንድንገኝ ተገቢውን ጥረት እንድናደርግ ያሳስበናል (2ጴጥ 3፡14)።

የይሁዳ መልእክት

የይሁዳ መልእክት የተጻፈው እማኞች ሳይሆኑ እማኞች መስለው በመግባት የሐሰት ትምህርት ከሚያስራጩ ሰዎች እንዲጠበቁና እንዲጠነቀቁ ለማሳሰብ ነበር። በይበልጥ ሁለተኛውን የጴጥሮስን መልእክት በሚመስለው በዚህ እጭር መልእክቱ ይሁዳ በማያዳግም ሁኔታ ሰቅዱሳን እንድ ጊዜ ስለተሰጠው እምነት በብርቱ እንዲጋደሉ እንባቢዎቹን በጥብቅ ያሳስባል።

የመልእክቱ ጸሐፊ

መልእክቱን የጻፈው ይሁዳ የተባለው እገልጋይ ሲሆን፣ በማቴ 13፡55፤ ማር 6፡3፤ ይሁዳ 1 ላይ የተጻፈው ቃል በሰማንነቱ እንደሚገልጸው የያዕቆብ ወንድምና የኢየሱስ ግማሽ ወንድም እንደነበር እንረዳለን። በሐዋ 1፡13 ላይ የተጠቀሰው የያዕቆብ ልጅ ይሁዳ እንዳልሆነ ግን መረዳት እስፈላጊ ነው። ይህን መልእክት የጻፈው ይሁዳ ከክርስቶስ ትንሣኤ በኋላ ጌታን ተቀብሎ በበዓለ ሃምሳ ዕለት መንፈስ ቅዱስን ከተቀበሉት እንዱ ነበር (ዮሐ 7፡5፤ የሐዋ 1፡14)

የመልእክቱ ይዘት

የይሁዳ መልእክት ከሁለተኛው የጴጥሮስ መልእክት ጋር ተመሳሳይነት እንዳለው ስመረዳት 2ጴጥ 3፡3 ላይ የተጻፈውን በይሁዳ ቁ.18 ላይ ከተጻፈው ጋር ማስተያየት ይረዳል። ምናልባት ይሁዳ የጴጥሮስን መልእክት ተመልክቶ ተመሳሳይ ችግር ለገጠማቸውና በግል ለሚያውቃቸው እማኞች ተመሳሳይ የሆነ መልእክት አስፈላጊ እንደሆነ ተሰምቶት ይሆናል እንደዚህ ያደረገው።

የሐሰት መምህራን ወደ ጉባኤያቸው ሾልከው እንደገቡ ይሁዳ በግልጽ የተረዳው ነገር በመሆኑ ሌላውን ጉዳይ እቋርጦ ስማስጠንቀቅ መልእክቱን በቶሎ ጸፈላቸው (ይሁዳ 3-4)። የጻፈላቸው እማኞች የሚኖሩበት ስፍራ ወይም እገር በመልእክቱ ውስጥ እልተጠቀሰም። የመጽሐፍ ቅዱስ ሊቃውንት እንደሚገምቱት እማኞቹ ይኖሩ የነበሩት በኢየሩሳሌም ወይም በእንጻኪያ ሊሆን እንደሚችል ነው።

ይሁዳ መልእክቱን የጻፈው የጴጥሮስ ሁለተኛው መልእክት ከተበራጨ በኋላ ሲሆን፣ የተጻፈው ኢየሩሳሌም ከመውደቋ በፊት ወደ 70 ዓ.ም ገደማ ሳይሆን እይቀርም። በመልእክቱ የሐሰት መምህራኑን ጠባይና የወደፊት ፍርዳቸውን ይገልጽና (1-16)፣ ለዚሁ ሁኔታ እንዴት ምላሽ መስጠት እንዳለባቸው ለእማኞቹ ይናገራል (17-25)።

የሚከተሰውን አከፋፈል እንደ መመሪያ በመጠቀም የይሁዳን መልእክት እንብብ።

የይሁዳ መልእክት፡ ክህደትን መዋጋት

I. የሐሰት መምህራን መኖር አደገኛነት 1-4 አንብብ
II. የሐሰት መምህራን መልክ 5-16 አንብብ
III. ስሐሰት መምህራን የተሰጠ መልስ 17-25 አንብብ

(4). የሐሰት መምህራኑን ባሕርይ በማስታወሻ ደብተርህ ላይ አስፍር።

ሀ. ቁ.4 እነዚህ ሰዎች ወደ ቤተ ክርስቲያን የገቡት እንዴት ነበር?
ስ. ቁ.4 የእግዚአብሔርን ጸጋ የስወጡት ስምን ነበር?
ሐ. ቁ.4 የካዱት ማንን ነበር?
መ. ቁ.8 የማይቀበሱት ምን ነበር?
ሠ. ቁ.16 ፉከራቸውና ትምክህታቸው ስስምን ነበር?
ረ. ቁ.19 የነደላቸው ምን ነበር?

(5). ይሁዳ በመልእክቱ አማኞቹ ስላሉበት ሁኔታ ሊያደርጉት የሚገባቸውን የተስያዩ ነገሮች ተናግሯል። ቁጥሩን ስባዶው ስፍራ በማስቀመጥ አብሮ የሚሄደውን መመሪያ እመልክት።

1. መንፈስ ቅዱስ
2. የሚጠራጠሩ ሰዎች
3. ለቅዱሳን የተስጠ እምነት
4. የእግዚአብሔር ፍቅር
5. የሐዋርያት ትንቢት

___ሀ. ተጋደሉ
___ስ. እስቡ
___ሐ. ጸልዩ
___መ. ራሳችሁን ጠብቁ
___ሠ. እንዳንዶችን እድኑ በፍርሃት ማሩ

እንደ ሁለተኛው የጴጥሮስ መልእክት፣ የይሁዳ መልእክትም ወንጌልን ስሚያጣሙሙና አማኞችን ስሚያስቱ ከበድ ያለ ማስጠንቀቂያ የያዘ ነው። ዛሬም እኛ እንደነዚህ ዓይነት ሰዎች ቢያጋጥሙን ሲያስገርመን እንደማ ይገባ ያሳስበናል። እንደዚህ ዓይነቱ ሁኔታ ሲያጋጥመን ይሁዳ በመልእክቱ እንደገለጸው የወንጌልን እውነት እጥብቀን በመያዝና የተታለሉትን ለመመለስ ሰምሀረት እጃችንን በመዘርጋት ሁኔታውን መቋቋም ይኖርብናል። ሰድል አድራጊነት በርሱ ዙፋን ፊት እስከንቀርብ ድረስ እግዚአብሔር ሲረዳንና ሊጠብቀን እንደሚችል ሰመገንዘብ እምነታችንን በእርሱ ላይ በማጽናት ከእንደዚህ ዓይነቱ ስህተት ርቀን እንደ ቃሉ መሠረት ለመኖር እንዲያስችለን የዘወትር ጸሎታችን ሲሆን ይገባል።

ሦስቱ የዮሐንስ መልእክቶች

ዮሐንስ በሦስቱም መልእክቶቹ አበክሮ የሚቃወመው የስህተት ትምህርት ለየት ያስ ሲሆን፣ ክርስቶስ በሥጋ አልመጣም በማስት ሐሰተኛ መምህራን የሚያስተምሩትን የሐሰት ትምህርት ነበር (2ዮሐ 7) ሦስቱም የዮሐንስ መልእክቶች የተጻፉት በሐሰት መምህራን ምክንያት ስእንደዚህ ዓይነቱ

የሐሰት ትምህርት የተጋለጡትን አማኞች ስለ ደነትና ስለ ክርስቲያናዊ ኑሮ ትምህርትና መመሪያ ለመስጠት ነበር።

የዓይን ምስክሩ ዮሐንስ

አንደኛ፣ ሁለተኛና ሦስተኛ ዮሐንስን የጻፈው ቀደም ሲል የዮሐንስ ወንጌልንና በኋላም የዮሐንስ ራዕይን መጽሐፍ የጻፈው ዮሐንስ ነበር። እንዳንድ ታሪካዊ ጽሑፎች እንደሚያመለክቱት በ70 ዓ.ም ኢየሩሳሌም ከፈራረስች በኋላ ዮሐንስ ወደ ኤፌሶን ሄዶ በኤፌሶንና በአካባቢዋ ሲያገለግል ኖረ። በኋላም በሮማው ንጉሥ በዶሚትያን ኋስኛ ዘመን 81-96 ወደ ፍጥሞ ደሴት ተስዶ በግዞት ቆየ። ንጉሡ ዶሚትያን ከሞተ በኋላ ዮሐንስ ከግዞቱ ተለቅቆ የጀመረውን እገልግሎት ስመቀጠል ወደ ኤፌሶን አካባቢ ተመለሰ። ሦስቱ የዮሐንስ መልእክቶች ተጽፈው ዮሐንስ ባገለገለባቸው ሰአስያ አካባቢ ስአብያተ ክርስቲያናትና ለአማኞች በመጀመሪያ የተላኩት በ85-90 ዓ.ም ባሉት ዓመታት መካከል ሳይሆን አይቀርም። ዮሐንስ የክርስቶስ ሕይወት የዓይን ምስክርና የቅርብ ወዳጅ እንደመሆኑ፣ የክርስቶስን በሥጋ መምጣት ክደው ሌሎችን ስማስካደ የሚፍጨረጨሩትን የሐሰት መምህራን የሚቃወማቸው በታላቅ ሐዋርያዊ ሥልጣን ነበር።

የሐሰት መምህራን

አማኞች እንዲጠነቀቁና እንዲጠበቁ ያስጠነቀቃቸው የሐሰት መምህራን ክርስቶስ ሥጋ ስብሶ ወደዚህ ዓለም የመምጣቱን እውነት አይቀበሉም። በእነርሱ እስተያየት መንፈስ ጥሩ ሲሆን ሥጋ ግን ክፉ ወይም መጥፎ ነው የሚል ግምት አላቸው። መልካምና ጥሩ የሆነው እምላክ እውነተኛ ስው ሰመሆን ራሱን ከአካላዊ ነገር ጋር አስተካከስ ማለት ፈጽሞ የማይታሰብ ጉዳይ እንደሆነ አድርገው አስተማሩ። አንዳንዶቹ፡- ኢየሱስ ሥጋ የለበስ ይመስላል እንጂ ለደቀ መዛሙርቱ የታየው በምትሃት እንጂ በሥጋ አይደለም አሉ። ሌሎቹ ደግሞ በጥምቀቱ ወቅት "የክርስቶስ መንፈስ" ስው በሆነው ኢየሱስ ላይ ከመጣ በኋላ ከመስቀሉ በፊት ትቶት ሄደ ይሉ ነበር። እነዚህ ሁለቱም ሃሳቦች ኢየሱስ በሥጋ የተገለጠ አምላክ እንደነበረ የሚናገረውን እውነት የካዱ ናቸው።

ከነዚህ የሀሰት መምህራን እንዳንዶቹ ደግሞ ያስተምሩ የነበሩት "ስው ልዩ ዓይነት የሆነ እውቀት በማግኘት ከዚህ ቁሳዊና አካላዊ ዓስም ወደ መንፈሳዊው ዓስም ለማምለጥ መጣርና መታገል አለበት" በማለት ነበር። ይህ የስህተት ትምህርት በእንግሊዘኛ ኖስቲሲዝም (Gnosticism) ተብሎ ይጠራል። እነዚህን የሐሰት ሃሳቦች በመቃረን ዮሐንስ ለዘላስም ሕይወት ዋስትና የሚሰጠው እውነተኛ እውቀት ምን እንደሆነ ይገልጻል (1ዮሐ 2:3፣ 3:10፣14፣ 5:20)። የክርስቶስን መለኮታዊነትና ስብአዊነት በመልእክቱ ያረጋግጣል (1ዮሐ 1:1-2፣2:22-23)።

1ኛ የዮሐንስ መልእክት

ሐዋርያው ዮሐንስ ዓላማ የነበረው ጻሐፊ ነበር። በመጀመሪያ ወንጌሉን ሲጽፍ እንደገለጸው የጻፈበት ዓላማ ሰዎች በክርስቶስ እምነው የዘላለምን ሕይወት እንዲያገኙ እንደሆነ በግልጽ ተናግሯል (ዮሐ 20:31)። በመጀመሪያው መልእክቱ ላይ ደግሞ መልእክቱን የጻፈው ሰዎች የዘላለም ሕይወት እንዳላቸው ያውቁ ዘንድ እንደሆነ በ1ዮሐ 5:13 ላይ ይናገራል። ሰዎች በክርስቶስ እምነው የዘላለምን ሕይወት እንዲያገኙና ሰዎች የዘላለም ሕይወት እንዳላቸው እንዲያውቁ በማለት የሚገልጻቸው እነዚህ ሁለት ዓላማዎች የተቀራረበ ግንኙነት አላቸው። ዮሐንስ የጌለገው አማኞች ከእግዚአብሔር ጋር ያላቸውን አዲሱን ግንኙነት በሚገባ እንዲገነዘቡ ለመርዳትና የድነት ዋስትናቸውን እንዲጨብጡ ሰማድረግ ነበር። በመልእክቱም ስሰ ክርስቶስ ባቀረባቸውም እውነቶች በሐሰተኛ መምህራን ምክንያት ለተነሡት ጥርጥሮች ተገቢውን መልሶች ይሰጣል።

6. ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ጥቅሶች በቅደም ተከትል ካነበብክ በኋላ የሚገልጡትን እውነትና የሚቃወሙትን የሐሰት ትምህርት በአጭሩ በማሰታወሻ ደብተርህ ላይ ግለጽ። የሚቃወሙት የሐሰት ትምህርት "ክርስቶስ በሥጋ አልመጣም" የሚል ከሆነ የሚቃወሙት ስህተት በሚለው ሥር "ቁጥር 1" ጻፍ። "ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅ ወይም ክርስቶስ አይደለም" የሚሰውን ከሆነ "ቁጥር 2" ጻፍ። ጥያቄ 1 ለምሳሌነት ተሠርቷል።

ጥቅሶች	የሚሰጡት እውነት	የሚቃወሙት ስህተት
1:1-3	ዮሐንስ ኢየሱስን ሰማ፣ ዳሰሰ አየ።	1
2:22		
3:23		
4:1-3		
4:15		

ሰለ ክርስቶስ እውነቶችን ጠለቅ እድርጎ ከማሰተማሩም በላይ ዮሐንስ አማኙ ሊኖረው ስለሚችል እርግጠኝነትና እውነተኛነት በመልእክቱ በጥልቀት ያስተምራል። የእርሱ እውቀት በምን ላይ እንደተመረኮዘ ይናገራል (1ዮሐ 1:1-4)። በብርሃን የመመላለስን አስፈላጊነት በማሰረዳት 1:5-2:14፣ አማኞች ዓለምን ከመውደድና በክርስቶስ ተቃዋሚ እንዳይስቱ የሚያስጠነቅቀው ክፍል እድርጎ ነው (2:15-27)። የእግዚአብሔር ልጆች መሆናቸውን እንዴት ለማወቅ እንደሚችሉም በማሰረዳት (2:28-3:10)፣ በእውነት ላይ መቆማቸውን ማወቅ የሚችሉበትን መንገድ ያብራራል (3:11-4:6)። በእውነት ላይ ያልቆሙትንም እንዴት ለይተው ለማወቅ እንደሚችሉ በማሰረዳት እርሰ በርሳቸው እንዲዋደዱ ትእዛዝ ይሰጣቸዋል (4:7-21)። ከእግዚአብሔር ጋር ሰላላቸውም ግንኙነት ዋስትና ይሰጣቸዋል (5:1-21)።

ከዚህ ቀጥሎ የተሰጠውን እከፋፈል እንደ መመሪያ በመጠቀም የመጀመሪያውን የዮሐንስን መልእክት እንብብ።

1ኛ ዮሐንስ፡ ዋስትና ለአማኞች

I. እውነትን በማወቅ የሚገኝ ዋስትና	1:1-4 እንብብ
II. በብርሃን በመመላለስ የሚገኝ ዋስትና	1:5-2:14 እንብብ
III. በእግዚአብሔር በመቀባት የሚገኝ ዋስትና	2:15-29 እንብብ
IV. ትክክለኛውን በማድረግ የሚገኝ ዋስትና	3:1-10 እንብብ
V. እውነትና ፍቅርን ስማሳየት የሚገኝ ዋስትና	3:11-20 እንብብ
VI. መንፈስ ቅዳስን በመቀበል የሚገኝ ዋስትና	3:21-4:6 እንብብ
VII. ክርስቶስን በማወቅ የሚገኝ ዋስትና	4:7-21 እንብብ
VIII. የእግዚአብሔርን ትእዛዝ በመጠበቅ የሚገኝ ዋስትና	5:1-12 እንብብ
IX. በክርስቶስ በመሆን የሚገኝ ዋስትና	5:13-21 እንብብ

(7). እውነተኛ የሆነውን መግለጫ ፊደሉን በመክበብ እመልክት።
ሀ. ዮሐንስ ወንጌሉንና መልእክቶችን የጻፈው ስለ ኢየሱስ ከሌሎች ምስክርነት ሰምቶ ነው።
ሰ. ዮሐንስ በመልእክቱ ያስጠነቀቃቸው የሐሰት መምህራን ኢየሱስ በሥጋ እንደመጣ አላመኑም።
ሐ. ዮሐንስ መልእክቶቹን የጻፈላቸው አማኞች ዋናው ችግራቸው ሰሰ እሕብ መገረዝ ወይም አለመገረዝ ነበር።

2ኛ የዮሐንስ መልእክት

ሁለተኛው የዮሐንስ መልእክት የተጻፈው ሰተመረጠችው እመቤትና ለልጆቹዋ እንደሆነ ከቁጥር አንድ ላይ ሰመረዳት እንችላለን (2ዮሐ 1)። በዚህ የተሰየመችው እንዲት እናትና ልጆች ሊሆኑ ይችላሉ ወይም ደግሞ እንዲት ቤተክርሰቲያንና ምዕመናን ሊሆኑ ይችላሉ። (ጳውሎስ በገላትያ 4:26 ሰምሳሌ "እናታችን" ያለውን ተመልከት) ያም ሆነ ይህ አማኞች በእውነትና በፍቅር እንዲመላለሱ በመምከር (ቁ. 1-6) የኢየሱስን በሥጋ መገለጥ የሚክደውን የክርስቶስ ተቃዋሚ በፍጹም እንዲቃወሙ ይነግራቸዋል (ቁ. 7-13)።

2ኛ ዮሐንስ፡ በእውነትና በፍቅር መመላለስ

I. የእግዚአብሔርን የፍቅር ሕግ መታዘዝ	1-6 እንብብ
II. ክርስቶስን የሚክዱትን ሐሰተኛ መምህራንን መቃወም	7-13 እንብብ

(8). በ2ዮሐ 9-10 ላይ በተጻፈው ቃል መሠረት አማኞች መቀበልና ማሰተናገድ ያለባቸው ሁሰንም ሰው ነውን? መልስህን አብራራ።

3ኛ የዮሐንስ መልእክት

ዮሐንስ ሦስተኛው መልእክቱን የጻፈው ጋይዮስ የተባለው የቤተ ክርስቲያን መሪ ሌሎችን በመርዳቱ ሊያመሰግነውና ዶዮጥራጢስ ከተባለ ተንኮለኛ ሰው እንዲጠበቅና እንዲጠነቀቅ ለማሳሰብ ነበር። መልእክቱ እንግዳ ተቀብሎ ስለማስተናገድ የሚናገር ቢሆንም፣ በዚህ ጉዳይ ላይ ዮሐንስ ሊገልጥ የፈለገው ለክርስቲያኖች የሚደረገውን የእንግድነት አቀባበል ነበር። አንዳንድ አማኞች ወንጌል ስለመስበክ በየስፍራው ይዘዋወሩ ስለነበር (3ዮሐ 8) በመልእክቱ የተናገረው እንደነዚህ ዓይነቶቹን ሰዎች ስለ መቀበልና ስለ ማስተናገድ አስፈላጊነት ነበር (3ዮሐ 7)።

ጋይዮስ አባል በሆነበት ቤተ ክርስቲያን የነበረ ዲዮጥራጢስ የተባለ የቤተ ክርስቲያን መሪ እነዚህን ሰዎች መቀበልና መርዳት አይፈልግም ነበር (ቁ. 9-10)። ጋይዮስ በወንጌል ምክንያት የሚዘዋወሩትን ወንድሞች ተቀብሎ በማስተናገዱ ዮሐንስ ለመልእክቱ እየደገፈ (3ዮሐ 1-8)፣ የዲዮጥራጢስን መጥፎ አድራጎት እንደሚያጋልጥ ይገልጻል (ቁ. 9-10)። ጋይዮስ በክርስትና ሕይወቱ እንዲበረታ አያበረታታ ዲሜጥሮስን ስእርሱ አደራ ይሰጠዋል (ቁ. 11-14)። ሦስተኛውን የዮሐንስን መልእክት ካነበብክ በኋላ የሚከተለውን መልመጃ አጠናቅ።

3ኛ ዮሐንስ፡ ክርስቲያናዊ እንግዳ አቀባበልን ተለማመድ

I. እንግዳ ተቀባይን ማመስገን	1-8 አንብብ
II. ትዕቢተኛ ተቃዋሚን ማስጠንቀቅ	9-10 አንብብ
III. መልካም ሠራተኛን መደገፍ	11-14 አንብብ

(9). በ3ዮሐ 8 ላይ በክርስቶስ ወንጌል ምክንያት በየሥፍራው የሚዘዋወሩትን አማኞች ተቀብለው የሚያስተናግዱ _____።

እንደኛው፣ ሁለተኛውና ሦስተኛው የዮሐንስ መልእክት "ኢየሱስ የሚወደው" ደቀ መዝሙር ምን ዓይነት እንደነበር ስማወቅ አድል ይሰጠናል (ዮሐ 21፡20)። ለዮሐንስ እውነትና ፍቅር ሊለያዩ የማይችሉ አብረው የሚሄዱ ነገሮች ናቸው። ፍቅር የሚያሳዩ እውነት ምን እንደሆነ የሚያውቁ ሰዎች ናቸው። እውነትን የሚያውቁ ሰዎች ደግሞ ፍቅርን የሚያሳዩ ሰዎች ናቸው። ዮሐንስ ስእነዚህ ሰሁለቱ ከፍተኛ ሥፍራ ይሰጣል። እነዚህ ሁለቱ ፍጹም መግለጫ ያገኙት በኢየሱስ ክርስቶስ በራሱ ነው (1ዮሐ 4፡16፤5፡20)።

ሦስቱ የዮሐንስ መልእክቶች ከሁለተኛው የጴጥሮስ መልእክትና ከይሁዳ መልእክት ጋር በመሆን የሐሰት ትምህርቶችን ለመከላከልና ለመቋቋም ጠንካራ መሠረት ይሰጡናል። እንዲሁም በቀድሞዋ ቤተክርስቲያን አንዳንድ ችግሮች በተነሡ ወቅት መሪዎቹ እንዴት ስመቋቋምና ምላሽ ስመስጠት እንደቻሉ እንድንገነዘብ ያደርጉናል። ከዚህም በተጨማሪ አማኞች

አስፈላጊውን እውነት ከማወቅ ባሻገር፣ አስተማሪዎች ነን ብለው የሚቀርቡትን እውነተኛ የክርስቶስ ተከታይ መሆናቸውን ለማወቅ መፈተን አስፈላጊ እንደሆነ የሚያሳይ ነው።

የቤተክርስቲያን ተስፋ
የክርስቶስ ዳግም መጽአት

የዮሐንስ ራዕይ፡

ዓላማ 2 በመልእክቱ ጎልተው ስለሚታዩት ነገሮች፡- ስለታሪካዊ መነሻው፣ ስለ አጻጻፍ ስልቱና በጠቅላላው ስለ መጽሐፉ፡ አስፈላጊውን ግንዛቤ ለማግኘት።

የዮሐንስ ራዕይ መጽሐፍ የጌታን በድል አድራጊነት መምጣት ቤተ ክርስቲያን በናፍቆት እንደምትጠባበቅ የሚያስረዳ ነው። አማኞች ኢየሱስ ክርስቶስን ጌታቸው አድርገው በቅድስና በመኖራቸው ምክንያት ስደትና መከራ ይደርስባቸው በነበረ ወቅት የተጻፈ ነው። የአሐፊው ሞና ትኩረት አማኞቹ በደረሰባቸው መከራና ስደት ውስጥ ሲያልፉ ተስፋቸውን አጥብቀው በመያዝ በእምነታቸው እንዲጸኑ ለመምከር ነበር።

የዮሐንስ ራዕይ በአዲስ ኪዳን ውስጥ የመጨረሻው መጽሐፍ ሲሆን፣ ለጠቅላላው መጽሐፍ ቅዱስ ተስማሚ ማጠቃለያና መደምደሚያ ነው። በከብቶች በረት ተወልዶ ተቀባይነት ያጣው አዳኝ ኢየሱስ ክርስቶስ አንድ ቀን እንደ ንጉሥ ሆኖ በታላቅ ኃይልና ክብር ወደ ምድር እንደሚመለስ ያትታል። የእግዚአብሔር ዓላማዎች ሙሉ በሙሉ እንደሚፈጸሙ የታወቀና የታመነ መሆኑ የመጽሐፉን ልዩ ትኩረትና ይዘት እንደዚሁም አተረጓጎም እያጠናን ስንሄድ የምንረዳው ጉዳይ ነው።

የመጽሐፉ ታሪካዊ መነሻ

ከመጽሐፉ ታሪካዊ መነሻ እንደምንረዳው አይሁዶች ዙተለያየ ወቅት በገዥዎቻቸው በሮማውያን ላይ ያምጹ ነበር። የሮም መንግሥት በ70 ዓ.ም. ኢየሩሳሌምን የደመሰሰውና ያፈራረሰው ይህንኑ አመጽ ለማፈንና ለማገድ ነበር። በዚሁ ወቅት ኢየሱስ እንደተነበየው በእሥራኤ አስደናቂ የነበረው ቤተ መቅደስ ጭምር ሳይቀር ፈራረስ (ማቴ 24:2)። ከዓመታት በፊት ኢየሱስ እንዳንድ ድርጊቶች ሲፈጸሙ ሲያዩ ከከተማይቱ ሸሽተው እንዲወጡ ለተከታዮቹ አስጠንቅቆአቸው ነበር (ማቴ 24:15-25)። በዚህ ወቅት ሳይሆን አይቀርም ዮሐንስ ወደ ኤፌሶን ሄዶ በአካባቢው ሲያገለግል የቆየው፣ ቀደም ሲል እንደጠቀስነው ወደዚያ የሄደውም በ69 ወይም በ70 ዓ.ም ይመስላል።

ከኢየሩሳሌም መውደቅ በኋላ ባሉት ዓመታት ሮማውያን በክርስቲያኖች ላይ የነበራቸው አስተያየት ከጥርጥር ወደ ጥላቻ ተስወጠ። ይህም ጥላቻ በመጀመሪያ የተገለጠው በ64 ዓ.ም ሮምን አቃጥለዋል በማለት

ክርስቲያኖቹን በመክሰስ ብዙዎችን በገደለው በንጉሥ ኔሮ ነበር። በኋላም ስደቱ መልኩን በመቀየር ለባሰሥልጣኖች ተገዙ (ሮሜ 13:1) በማለት ቀደም ሲል ያስተምሩ የነበሩት ክርስቲያኖች አሁን ለእነዚህ ባለሥልጣኖች መገዛትና መታዘዝ አስቸጋሪና የማይቻል ሆኖ አገኙት።

ዶሚቲያን የተባለው የሮማ ንጉሥ (81-96 ዓ.ም) እንደ አምላክ እንዲሰገድለት በማስገደድ እንሰግድም ያሉት እንዲሰደዱ አደረገ። ከነዚህም ከተሰደዱት መካከል ዮሐንስ አንዱ ሳይሆን አይቀርም። በንጉሥ ዶሚቲያን በኋለኛው ዘመን ዮሐንስ በስደት ወደ ፍጥሞ ደሴት የሄደበት ምክንያት ይህ ሳይሆን አይቀርም፤ (ራዕ 1:9)። በዚያ ደሴት ላይ ሳለ በሮም መንግሥት ጨካኝ እገዛዝ ሥር በጭቆና ላይ ለነበሩት ሰአሰያ አማኞች የሚሆን መልእክት እግዚአብሔር ሰጠው። መልእክቱ አያንዳንዱ አማኝ ሊገነዘበው የሚያስፈልግና ክርስቶስንና የአርሱን የመጨረሻ ድል በውሰጡ የያዘ በመሆኑ፣ መልእክቱ ለሁሉም አማኞች የሚሆን እንጂ ለአነርሱ ብቻ አልነበረም።

(10). _____ ከተደመሰሰች በኋላ፣ የሮም መንግሥት በዶሚትያን እየተመራች ሳለች፣ ዮሐንስ ተሰዶ ወደ_____ደሴት አስከሄደበት ጊዜ ድረስ በ_____ _____አካባቢ ያገለግል ነበር። ዮሐንስ የዮሐንስ ራዕይን በሚፅፍበት ወቅት ሮማውያን በክርስቲያኖች ላይ የነበራቸው አስተያየት ከጥርጥር ወደ_____ተለወጠ። ንጉሥ ዶሚቲያን _____ _____ትዕዛዝ ከማውጣቱ የተነሣ ክርስቲያኖች ንጉሡን መታዘዝና መገዛት አልቻሉም።

የመጽሐፉ ልዩ ሁኔታ

ዮሐንስ የተቀበሰውን መልእክት በጽሑፍ ያቀረበው በራዕይ መልክ ሲሆን ይህም አቡቀለምሲስ (apocalyptic) እሳፃፍ ይባላል። በብሉይ ኪዳን የዚህ ዓይነት አቀራረብ ያለው የትንቢተ ዳንኤል መጽሐፍ ነው። የዚህ ዓይነቱ አቀራረብ የሚታዩ ነገሮችን ከቀጥታና ከመደበኛ ትርጉማቸው ሌላ ሚስጥራዊ ትርጉም ያላቸው መግለጫዎች ናቸው። ለምሳሌ ያህል በራዕ 1:12-13 ላይ ዮሐንስ ኢየሱስን በሰባት የወርቅ መቅረዞች መካከል እንዳየው ይናገራል። ጥቂት ወረድ ብለን ስናነብ እነዚህ ሰባት የወርቅ መቅረዞች ዮሐንስ መልእክቱን እንዲጽፍላቸው የተነገረው ሰባቱ አብያተ ክርስቲያናት እንደሆኑ ይነግረናል (1:10-11፣20)። በእንደዚህ ዓይነቱ የአጻጻፍ ስልት (በአቡቀሰምሲስ) እንዳንድ ቁጥሮች ደግሞ ከቀጥታ ትርጉማቸው ባሻገር ሌላ ትርጉም ሊኖራቸው ይችላል። ለምሳሌ ያህል ቁጥር ሰባት ስሰ ፍጹምነት የሚናገር ሲሆን፣ ሰሰባቱ አብያተ ክርስቲያናት የተጻፈው 1:11፣ መልእክቱ ለእነርሱ ብቻ ሳይሆን፣ ለጠቅላላው አብያተ ክርስቲያናት እንደሆነ የሚያመለክት ነው። ሰባት ማኅተሞችና ሰባት መሰከቶች እንደዚ ሁም ሰባት መቅሰፍቶች መኖራቸው ደግሞ የእግዚአብሔር ፍርድና ዓላማ በምድር ላይ እንደሚፈጸም የሚያመለክት ነው (6:1፤8:2፤ 15:1፤ 18:1)።

ከዚህም በተጨማሪ የዮሐንስ ራዕይ መጽሐፍ ከብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ጋር የቅርብ ግንኙነት ያለው በመሆኑ፣ ዮሐንስ የብሉይ ኪዳን መጻሕፍትን ደህና አድርጎ ያውቅ እንደነበር የሚያመለክት ነው። ዮሐንስ በመልእክቱ ከተለያዩ የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት የጠቀሳቸው ወደ 275 የሚያህሉ ምንባቦች ይገኛሉ። እነዚህን የሱሉይ ኪዳን ምንባቦች ለመጥቀስ ያህል የጠቀሳቸው ብቻ ሳይሆን የእግዚአብሔር መንፈስ የገለጠለትን ትንቢታዊ እውነቶች በኃይልና በሥልጣን ለማስተላለፍ ከሥዕላዊ ምሳሌዎች ጋር በማቀናጀት አዲስ መንገድ መጠቀሙን ያስረዳል።

(11). ከዘፍ 2:9፤3:22-24 እና በራዕ 22:1-2 ላይ ስሰ ሕይወት ዛፍ የተሰጠውን ገለጻ ካነበብክ በኋላ፣ የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልስ በማስታወሻ ደብተርህ ላይ አስፍር።

ሀ. በዘፍ 3:22-24 ላይ የተጻፈው ቃል እንደሚነግረን፣ አዳምና ሔዋን በኃጢአት ከወደቁ በኋላ፣ ከሕይወት ዛፍ ፍሬ እንዲበሉ እንዳልተፈቀደላቸው ነው። ሐዋርያው በራዕ 22:2 ላይ ስሰ ሕይወት ዛፍ ፍሬ የሚናገረው ምንድን ነበር?

ለ. ለዚህ ልዩነት ምክንያቱ ምን ይመስልሃል?

(12). ከዚህ ቀጥሎ ከዮሐንስ ራዕይ መጽሐፍ የተወሰዱ አራት ጥቅሶች ሰፍረዋል። የአቡቀለምሲስ (apocalyptic) አሳፃፍ ምሳሌ የሆኑትን ፊደሱን በማክበብ አመልክት።

ሀ. እንግዲህ ይህን የትንቢት ቃል የሚያነብ ብፁዕ ነው (1:3)።

ለ. ከዙፋኑም መብረቅና ድምፅ፣ በዙፋኑ ፊት ሰባት መብራቶች ይበሩ ነበር፣ እነዚህም ሰባቱ የእግዚአብሔር መናፍስት ናቸው (4:5)።

ሐ. ከዚያም አንድ አውሬ ከባህር ሲወጣ አየሁ፣ አርሱም አሥር ቀንዶችና ሰባት ራሶች ነበሩት (13:1)።

መ. እነሆ፣ ቶሎ እመጣለሁ፣ ዋጋዬ በእኔ ዘንድ አሰ፣ ሰእያንዳንዱም እንደ ሥራው መጠን እከፍለዋለሁ (22:12)።

የመጽሐፉ ይዘት

የዮሐንስ ራዕይ መጽሐፍ ዮሐንስ ባያቸው አራት ራዕዮች ሊከፈል ይችላል። እያንዳንዱ ራዕይ የሚጀምረው፦ በመንፈስ ነበርኩ ወይም በመንፈስ ወሰደኝ በሚል ቃል እንደሆነ ከራዕይ 1:10፤ 4:2፤ 17:1-3፤ 21:9-10 ላይ ለመረዳት እንችላለን።

የመጀመሪያው ራዕይ በራዕይ 1:10-3:22 ላይ የተጻፈው ሲሆን፣ ዮሐንስ በአብያተ ክርስቲያናት መካከል ኢየሱስን አየ። አብያተ ክርስቲያናቱ ዮሐንስ ኢየሩሳሌምን ትቶ ከሄደ በኋላ ባገለገለበት በትንሻ እስያ በኤፌሶን አካባቢ ስለነበሩ፣ ዮሐንስ ከእነዚህ አብያተ ክርስቲያናት ጋር ግንኙነት ነበረው። ክርስቶስ ሰለ አያንዳንዱ ቤተክርስቲያን ባሕርይና ሁኔታ በመግለጥ

ለእነዚህ አብያተ ክርስቲያናት ተስማሚ የሆኑ መልእክቶችን ለዮሐንስ ሰጠው። ለምሳሌ ያህል በራዕ 2:8 ላይ ለሰምርኔስ ቤተክርስቲያን የተናገረው "ፊተኛውና መጨረሻው እንዲህ ይላል" በማለት ሲሆን፣ በ3:14 ላይ ለሎዶቅያ ቤተክርስቲያን የተናገረው ደግሞ "የታመነውና እውነተኛው ምስክር እንዲህ ይላል" በማለት ነበር።

ሁለተኛው ራዕይ በራዕይ 4:1-16:21 ላይ የተጻፈው ሲሆን፣ ዮሐንስ በሰማይ የእግዚአብሔርን ዙፋን ተመለከተ። በእግዚአብሔር እጅ የነበረውንም መጽሐፍ ለመክፈት ክርስቶስ የተገባው የእግዚአብሔር በግ እንደሆነ አየ። የእያንዳንዱንም መጽሐፍ ማኅተም ይዘት ዮሐንስ ገለጸ። ስባተኛው ማኅተም ሰባቱን መለከቶች ያካተተ ነበሩ። ከዚያም በማስከተል ሰባት የቁጣ ጽዋዎች ወይም የፍርድ መቅሰፍቶች ነበሩ። ከሰባቱ ማኅተሞች፣ መለከቶችና መቅሰፍቶች ጋር የተያያዙት ድርጊቶች የሚያሳዩት በዓለም ላይ የእግዚአብሔርን ፍርድ ሁኔታና ለተዋጁት ያለውን ፈቃዱን ነው። በዚህ ራዕይ ላይ ክርስቶስ የሚታየው የእግዚአብሔርን ዓላማዎች በተግባር ላይ ለማዋልና እንዲፈጸም ለማድረግ ሥልጣን ያለው ሆኖ ነው።

ሦስተኛው ራዕይ በራዕ 17:1-21:8 ላይ የተጻፈው ሲሆን፣ በዚህ ራዕይ ዮሐንስ ክርስቶስን ያየው የምድርን ክፉ ነገሥታትና ሠራዊቶቻቸውን ሁሉ ድል አድራጊ ሆኖ ነው። ስለ ባቢሎን የሀዘን እንጉርጉሮና ልቅሶ ሰማ የደረሰባትንም ጥፋት ተመለከተ። ከዚያም በተጨማሪ የስይጣንን የመጨረሻ ጥፋትና የሙታንን ፍርድ ከተመለከተ በኋላ አዲሲቱን ሰማይና አዲሲቱን ምድር አየ። በዚህ በሦስተኛው ራዕይ ላይ ክርስቶስን የሚያሳየው የዓለምን ታሪክ ወደ መጨረሻው ፍጻሜ የሚያመጣው ድል አድራጊ እንደሆነ ነው።

አራተኛው ራዕይ (ራዕ 21:9-22:5) ላይ የተጻፈው ሲሆን፣ በዚህ ራዕይ ዮሐንስ ያየው የክርስቶስ ሙሽራ የሆነችውን አዲሲቱ ኢየሩሳሌምን ነበር። በዚህ ራዕይ ስማቸው በሕይወት መጽሐፍ የተጻፉ ሁሉ የሚኖሩባት ከተማና ክርስቶስ የከተማዋ መቅደስና ብርሃን ሆኖ ነው የታየው።

የሚከተለውን አከላፈል እንደ መመሪያ በመጠቀም የዮሐንስ ራዕይን መጽሐፍ አንብብ።

የዮሐንስ ራዕይ፡ ድል አድራጊው ክርስቶስ

I. መግቢያ፡ ሠላምታና ውዳሴ	1:1-8 አንብብ
II. የመጀመሪያው ራዕይ፡ ክርስቶስ ለአብያተ ክርስቲያናት ይናገራል።	1:9-3:22 አንብብ
III. ሁለተኛው ራዕይ፡ ክርስቶስ የዓለምን ሁኔታ ይቆጣጠራል።	4:1-16:21 አንብብ
IV. ሦስተኛው ራዕይ፡ ክርስቶስ የክፋትን ኃይላት ያሸንፋል።	17:1-21:8 አንብብ

V. አራተኛው ራዕይ፡ ክርስቶስ በዙፋኑ ላይ ይነግሣል።	21:9-22:5 አንብብ
VI. መደምደሚያ፡ ምክርና ጥሪ	22:6-21 አንብብ

(13). በዮሐንስ ራዕይ መጽሐፍ ላይ በሰፈሩት አራት ራዕዮች መሠረት ለሚከተሉት ጥያቄዎች በማሰታወሻ ደብተርህ ላይ አጭር መልስ ስጥ፤

ሀ. የመጀመሪያው ራዕይ፡- ለሰባቱ አብያተ ክርስቲያናት በተናገረው መልእክት ውስጥ ክርስቶስ ተስፋ የገባው ለማን ነበር? (ምዕራፍ 2-3)

ለ. ሁለተኛው ራዕይ፡- መጽሐፉን ለመክፈት ክርስቶስ ብቻ የተገባው ለምን ሆነ? (ምዕራፍ 5)

ሐ. ሦስተኛው ራዕይ፡- ስይጣንን ለማሰርና ወደ ጥልቁ ጉድጓድ ለመጣል ስንት መላእክት አስፈለጉ? (ምዕራፍ 20)

መ. አራተኛ ራዕይ፡-ወደ ቅድስቲቱ ከተማ ሊገቡ የሚችሉ እነማን ናቸው? (ምዕራፍ 21)

የመጽሐፉ አተረጓጎም

የዮሐንስ ራዕይ መጽሐፍ አቀራረቡና ትምህርታዊ ይዘቱን በቀላሉ ለመረዳት ያስቸግራል። ስለ ትርጉሙ ሰዎች ለዓመታት የተለያዩና አንዳንድ ጊዜም ተቃራኒ የሆኑ ሃሳቦችንና አስተያየቶችን ይዘው ቆይተዋል። በዚህ ክፍል ውስጥ የመጽሐፉን ይዘት በሚመለከት አራት የአተረጓጎም መንገዶች ከተመለከትን በኋላ፡ መጽሐፉ ለመጀመርያዎቹ አንባቢዎችም ሆነ ለአሁኑ ዘመን ያዘለውን መልእክት እንመለከታለን።

1. ወቅታዊ

የወቅታዊውን አተረጓጎም የሚደገፉ የዮሐንስ ራዕይ ለተጻፈበት ጊዜና ዘመን ብቻ የሚያገለግል እንደሆነ አድርገው ይመለከቱታል። በእነርሱ አስተሳሰብ የዮሐንስ ራዕይ መጽሐፍ ቤተክርስቲያን ፈሪሐ - እግዚአብሔር ካልነበረው ከሮም መንግሥት ኃይል ጋር በወቅቱ የነበራትን ትግል ጉልህ አድርጎ የሚያሳይ እንጂ ሰለ ወደፊቱ ትንቢታዊ የሆነ አመልካችነት ምንም የለውም። ይህ አተረጓጎም መጽሐፉ ለመጀመርያዎቹ አንባቢዎች ያለውን መልእክት በማቅረብ ረገድ ጥሩ ጎን ያለው ሲሆን፡ ዮሐንስ ያያቸውና ገና ያልተፈፀሙና ወደፊት የሚፈጸሙ የኢየሱስ ከሰማዕታቱ ጋር አንደ መንገሥ ያሉ (ራዕ. 20:4-6) ራዕዮችን ቦታ ሰለማይሰጥ ደካማ ጐን አለው።

2. ሃሳባዊ

ይህን አተረጓጎም የሚደግፉ የዮሐንስ ራዕይ በክፋትና በደግነት መካከል በመካሄድ ላይ ያለውን የማያቋርጥ ትግልና ቅራኔ የሚያሳይ ተምሳሌታዊ መግለጫ ነው ብለው ያምናሉ። የመጽሐፉም አውነተኛ ዓላማ የእግዚአብሔርን ባሕርይና የአዳኙን የክርስቶስን ኃይል ለመግለጥ እንደሆነ

ይናገራሉ። ይህ አስፈላጊ ዓላማ ቢሆንም፣ በመጽሐፉ ላይ የሰፈሩት ተምሳሌቶች ወደ ፊት ስለሚፈጸሙ የተወሰኑ ድርጊቶች እንደሚያመለክቱ ስለማያምኑ አተረጓጎሙ የራሱ የሆነ ችግር አለው።

በትንቢተ ሕዝቅኤልና በዳንኤል ላይ እንደተስጡት ተምሳሌታዊ አገላለጾች የመሳሰሉ ብዙ የመጽሐፍ ቅዱስ ትንቢቶች መፈጸማቸውን ከማምት ውስጥ አያስገባም።

3. ታሪካዊ

ይህን አተረጓጎም የሚደግፉ የዮሐንስ ራዕይ መጽሐፍን ተምሳሌቶች የሚመለከቷቸው ከበዓሉ ሃምሳ ቀን እንሥቶ እስከ ክርስቶስ ምጽአት ድረስ ያለውን የቤተክርስቲያን ታሪክ ሂደት የሚያሳይ አድርገው ነው። በዚህ አተረጓጎም የመጽሐፉ ተምሳሌቶች በቤተክርስቲያን ላይ ተጽእኖ ካላቸው ታሪካዊ ድርጊቶች ጋር የተያያዙ ናቸው። አንዳንዶቹም ታሪካዊ ድርጊቶች ቀደም ብለው የተፈጸሙ አድርገው ይቆጥሯቸዋል። (ስምሳሌ ያህል በምዕራፍ 6 ላይ የተገለጹትን ማኅተሞች በመጀመሪያው መቶ ዓመት የክርስቲያኖች አሳዳጅ የነበረው የሮማን መንግሥት መውደቅን የሚያመለክቱ አድርገው ይተረጉሙታል።) በዚህ ዓይነቱ የአተረጓጎም መንገድ አንድ ተምሳሌት በርከት ያሉ ድርጊቶችን ወይም ግለሰቦችን የሚወክል ስለሚሆን ይህን አተረጓጎም የሚከተሉ ራሳቸው እርስ በርሳቸው ብዙ አለመግባባት እንዲኖራቸው ያደርጋል። በዚህም ምክንያት ስለ መጽሐፉ መልእክት ተጨባጭ መረዳት ላይ እንዳይደርሱ ያደርጋቸዋል።

4. ትንቢታዊ

ይህን አተረጓጎም የሚከተሉ ለዮሐንስ የተሰጡት አብዛኛዎቹ ራዕዮች ወደ ፊት ስለሚፈጸሙ ድርጊቶች እንደሆኑ አድርገው የሚያምኑ ናቸው። ከምዕራፍ 4 - 19 የተገለጹት ከክርስቶስ መመለስ ጥቂት ቀደም ብሎ በሚኖሩት ዓመታት ውስጥ የሚፈጸሙ ሲሆን፣ ይህም "ታላቁ የመከራ ዘመን" ተብሎ ይጠራል። በዚህ አተረጓጎም ስምሳሌ ያህል በምዕራፍ 13 ላይ የተጠቀሰው አውሬ የሚያመለክተው የዓለምን መንግሥታት ሲሆን፣ በምዕራፍ 17 ላይ የተጠቀሰችው አመንዝራዋ ሴት (ባቢሎን) የምታመለክተው ክርስቶስ በሚመለስበት ጊዜ የሚኖረውን የሃሰት ሃይማኖቶች ነው። አንዳንድ የትንቢታዊ አተረጓጎም አራማጆች በምዕራፍ 2 እና 3 ላይ የተጠቀሱት ሰባቱ አብያተ ክርስቲያናት የሚያመለክቱት ሰባት የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ዘመናትንና ዮሐንስ የጻፈላቸውን ሰባቱን የእስያ አብያተ ክርስቲያናት አድርገው ነው።

(14). ስለ ዮሐንስ ራዕይ መጽሐፍ አተረጓጎም ቁጥሩን በተስጠው ስፍራ በማስቀመጥ አብሮ የሚሄደውን አዛምድ።
1) ወቅታዊ 2) ሃሳባዊ 3) ታሪካዊ 4) ትንቢታዊ

--ሀ. በዮሐንስ ራዕይ ያሉት ድርጊቶች ከበዓለ ሃምሳ ቀን እንሥቶ እስከ ክርስቶስ ምጽአት ድረስ ያለው የቤተ ክርስቲያን ታሪክ የወቅቶች አከፋፈል ናቸው።
--ለ. በዮሐንስ ራዕይ የተገለጡት ድርጊቶች ሁሉ ከተጻፉ በኋላ በአጭር ጊዜ ውስጥ ተፈጽመዋል።
--ሐ. በምዕ. 18 የተገለጸው የባቢሎን መውደቅ ክርስቶስ ከመመለሱ ጥቂት ቀደም ብሎ ይፈጸማል።
--መ. በምዕራፍ ዘጠኝ ላይ የተጠቀሱት አንበጦች ለዘመናት የሚካሄደው የክፋትና የደግነት ጦርነት ምሳሌዎች ናቸው።
--ሠ. በምዕራፍ 11 ላይ የተጠቀሱት ሁለቱ ምስክሮች በታላቁ የመከራ ዘመን ትንቢት ይተነብያሉ።

የዮሐንስ ራዕይ መጽሐፍ አብዛኛው በተለይም ከምዕራፍ 4-22 ያለው መተርጎም ያለበት በትንቢታዊ አተረጓጎም መሆን እንዳለበት በርካታ ክርስቲያኖች ያምናሉ። የዮሐንስ ራዕይ ትንቢቶችን ከሌሎቹ የመጽሐፍ ቅዱስ ትንቢቶች ጋር እንዲስማሙ ስለሚያደርግ ምናልባት ከሁሉም የተሻለው ይህ ትንቢታዊ አተረጓጎም የተባለው ነው። ይህን የአተረጓጎም መንገድ የሚይዙ የዮሐንስ ራዕይ ትንቢቶች የበፊቱን ትንቢቶች ትርጉም እንዴት ሊያሰፋፉ እንደሚችሉ ለማሳየት ይችላሉ።

ስምሳሌ ያህል:- ዘዳን 7:13 እና ዘሕዋ 1:11 ላይ ኢየሱስ ወደ ምድር እንደሚመለስ ይነግረናል። በራዕ 19:11-21 እና በራዕይ የሚገኙ ሌሎች የተለያዩ ምንባቦች እንዴት እንደሚመለስና ሲመለስም ምን እንደሚፈጸም ይበልጥ ዝርዝሮችን ሊሰጥ የሚችለው የትንቢታዊ አተረጓጎም ነው። በተጨማሪም የትንቢታዊ አተረጓጎም የሚያሳየን ዮሐንስ ስለ ክርስቶስ መምጣት፣ ስለሙታን ትንሣኤና ስለ ዳኑትና ስላልዳኑት ሰዎች የመጨረሻ መለየት ያየው ራዕይ ዝም ብሎ ሃሳቦችን ብቻ የሚያመለክት ሳይሆን፣ በእርግጥ የሚፈጸሙ እውነተኛ ድርጊቶችን የሚያሳይ ነው።

በዘመኑ ለነበሩት ያዘለው መልእክት

በትንሽዋ እስያ ለነበሩት አብያተ ክርስቲያናት የዮሐንስ ራዕይ የማበረታቻና የምክር ቃል ያዘለ መጽሐፍ ነበር። ሰባቱ ደብዳቤዎች በግልጥ የሚያሳዩት አንዳንድ አማኞች የሐሰት ትምህርት በመቀበል ለመንፈሳዊ ነገር ግዴለሾች መሆን ጀምረው እንደነበር ነው (ራዕ 2:4፣ 14-16፣ 20፤ 3:1-3፣ 15-18)። ክርስቶስ እነዚህን አማኞች ለእርሱ ትምህርት ተገቢውን ምላሽ በመስጠትና ሕይወታቸውን ለእርሱ አገልግሎት በመስጠት ሕይወታቸውን እንዲያድሱ እነዚህን አማኞች ይመክራቸዋል።

አንዳንዶቹ አማኞች ደግሞ በከባድ ስደት ላይ እንደነበሩ መልእክቶቹ ያሳያሉ (2:3፣9፣13)። እግዚአብሔር አንድ ቀን ክፋዎችን እንደሚቀጣና ለታማኞች ደግሞ ተገቢውን ሽልማት እንደሚሰጥ በመጽሐፉ ውስጥ የሰፈሩት ትንቢቶች እነዚህን አማኞች ያበረታታቸዋል። በራዕይ መጽሐፍ

ውስጥ የቀረቡት አንዳንዶቹ ምሳሌዎች ምናልባት እነዚህ አማኞች ለይተው የሚያውቋቸውን ድርጊቶችን ወይም ስዎችን የሚያመለክቱ ሊሆኑ ይችላሉ። ለምሳሌ በምዕራፍ 13 ላይ ያዩት እውሬ ተምሳሌትነቱ ያሳድዳቸው የነበረውን የሮማን መንግሥት ይመስላል። በእግዚአብሔር ዘንድ ጸሎታቸውና ስቃያቸው ሁሉ የታወቀ እንደሆነ ይረዳሉ (6:9-11፣ 8:4፤14:13)። ስማዕታት ከክርስቶስ ጋር እንደሚነግሡና (20:4)፣ እንባዎችን ሁሉ ከዓይኖቻቸው እግዚአብሔር ራሱ እንደሚያብስ አወቁ (21:3-4)። እግዚአብሔር እውሬውን ስለሚቀጣ እስከዚያው ድረስ በመታገስና በታማኝነት መቆየት እንደሚያስፈልግ በትንቢቱ በኩል ተነገራቸው (13:10፣ 20:10)።

ለአሁኑ ዘመን የያዘው መልእክት

የዮሐንስ ራዕይ ለመላው ቤተ ክርስቲያን የቀረበ መልእክት በመሆኑ ባሬም ለእኛ የሚሆን መልእክት የያዘ መጽሐፍ ነው። መጽሐፉ ስሚስጠን ማስጠንቀቂያ፣ ምክርና የማበረታቻ ቃል በሙሉ ልባችን በመቀበል ተገዢውን ምላሽ መስጠት ይገባናል። እንደ ኤፌሶን ክርስቲያኖች ንስሐ መግባትና ስክርስቶስ ያለንን ታማኝነት ማደስ የሚያስፈልግበት ጊዜ ይኖር ይሆናል (ራዕ 2:4-6)። እንደ ስምርኔስ ክርስቲያኖች ደግሞ በመከራና በድህነት የምናልፍበት ጊዜ ይኖር ይሆናል (2:8-11)። የዮሐንስ ራዕይ መጽሐፍ፡ ስለ ዘላለም ቤታችን በግልጽ በማሳየትና አንድ ቀን እግዚአብሔር አንባን ሁሉ እንደሚያብስ ስስሚነግረን በእንደዚህ ዓይነቶቹ ጊዜያት በራዕይ መጽሐፍ፡ የተጻፉት ተስፋዎች ታላቅ መጽናናትን ሊስጡን ይችላሉ (21:3-4፤22:3-5)።

አንዳንዶቹ የዮሐንስ ራዕይ ትንቢቶች ከተጻፉ በኋላ ወዲያው የሚፈጸሙትን ትንቢቶች የሚገልጹ ቢሆንም ለእኛም አስፈላጊ መሆናቸውን መዘንጋት የስብንም። ድርጊቶቹ የሚፈጸሙትም በዓስም መጨረሻ ላይ እንደሆነ አንዳንዶቹ የሚያመስክቱ፡ ናቸው። እነዚህ ትንቢቶች እጥፍ ወይም ድርብ ፍጻሜ አንዳላቸው አንደ ሌሎቹ የመጽሐፍ፡ ቅዱስ ትንቢቶች ዓይነት ናቸው። ለምሳሌ በዘፍ፡ 46:4 ላይ እና 50:24 ላይ የያዕቆብ ዘር አንድ ቀን ከግብፅ እንደሚወጡ ትንቢት ይነግረናል። ይህ ትንቢት ሙሴ አስራኤላውያንን መርቶ ከግብፅ ባወጣቸው ጊዜ የተፈጸመ ሲሆን (ዘጸ 12:31-42)፣ ከብዙ ዓመታት በኋላ ይኸው ትንቢት በድጋሚ የተፈጸመው ሌላው የያዕቆብ ዘር ኢየሱስ ክርስቶስ ከግብፅ በወጣ ጊዜ ነበር (ሆሴ 11:1፣ ማቴ 2:15)።

በተመሳሳይ መንገድ እንዳንዶቹ የዮሐንስ ራዕይ ትንቢቶች እጥፍ፡ ፍጻሜ ይኖራቸዋል። ስምሳሌ በምዕራፍ፡ 13 ላይ የተጠቀሰው የአውሬው ትንቢት ሁለት ነገሮችን እንደሚያመስክት ብዙ የመጽሐፍ፡ ቅዱስ ተማሪዎች ያምናሉ። 1) ዮሐንስ መጽሐፉን በጻፈበት ወቅት የነበረውን የሮም መንግሥት የሚያመለክት ሲሆን፣ 2) ክርስቶስ ከመመስሱ በፊት በሚኖረው ክፍለ ጊዜ የሚ ቆጣጠረውን የዓለምን ኃይል ነው። ይህ ትንቢት ለእኛ ማስጠንቀቂያ ሲሆን፣ ስእግዚአብሔር ብቻ የሚገባውን

እምልኮ ለሌላ እንድናቀርብ ለሚፈልግ ኃይል እንዳንዘረክክ መጠንቀቅ ይገባናል (13:5-8፤15:2)። በምዕራፍ 20-22 እንዳሉት ዓይነት የራዕይ መጽሐፍ፡ ትንቢቶች ስለ ዘለዓለምና ስለ ዓስም መጨረሻ የሚናገሩ ስስሆኑ እንድ ፍጻሜ ብቻ ይኖራቸዋል።

(15). ድርብ ፍጻሜ ያላቸው ወይም ሊኖራቸው የሚችል ትንቢቶች

ሀ. እንድ ትርጉም ብቻ ያላቸው ትንቢቶች ናቸው።
ለ. በብሉይ ኪዳን ቢያንስ ሁስት ጊዜ ይጠቀሳሉ።
ሐ. በጊዜ ገደብ የተለያዩ ሁስት ተመሳሳይ ድርጊቶችን የሚያመለክት ነው፡
መ. ስክርስቲያኖች አንድ ትርጉም ሲኖረው፣ ክርስቲያን ላልሆኑ ደግሞ ሌላ ትርጉም ያስው ነው።

የዮሐንስ ራዕይ ትንቢቶችን ለመረዳት ብዙ ጊዜ አስቸጋሪ መሆኑ ሊያስገርመን አይገባም። እንደሌሎቹ የመጽሐፍ፡ ቅዱስ ትንቢቶች የፍጻሜአቸው ጊዜ ሲደርስ ትርጉማቸው ግልጽ እየሆነ እንደሚመጣ በማመን መጠባበቅ እንችላለን። የዮሐንስ ራዕይ መጽሐፍ፡ የሚያቀርበው ድል አድራጊው ክርስቶስ፣ ስለ ሐስተኞች የሚለጠው ማስጠንቀቂያና ስለ ቅድስና ኑሮ የሚስጠው ምክር እንደዚሁም ስለ ሕብረት የሚያቀርበው ጥሪ በየትም ቦታ ያሉ ክርስቲያኖች ሊገነዘቡት የሚችሉት ነው።

(16). የዮሐንስ ራዕይ መጽሐፍን ስመረዳት ትንቢታዊ አተረጓጎም የተሻለ የሆነው

ሀ. የተገለጹት ድርጊቶች በሙሉ ከስባቱ የእስያ ታሪካዊ አብያተ ክርስቲያናት ጋር እንደ ግንኙነት እንደ ነበራቸው ስለሚገልጽ ነው።
ለ. ከበዓስ ሃምሳ ዕለት እንሥቶ እስከ አሁን ድረስ ያለውን የቤተክርስቲያን ታሪክ ዝርዝር ገለጻ ስለሚሰጥ ነው።
ሐ. አብዛኛዎቹ ትንቢቶች በክፋትና በደግነት መካከል ያለው ውጊያ ተምሳሌታዊ መግለጫዎች መሆናቸውን ስለሚያረጋግጥ ነው።
መ. ቀደም ያሉ የመጽሐፍ ቅዱስ ትንቢቶችን ለማብራራት ትንቢቶቹ በእንድ ላይ የሚስጡትን ትርጉም ስለሚያሳይ ነው።

(17). በዚህ ትምህርት እንደተጠቀሰው ስለ ዮሐንስ ራዕይ መጽሐፍ ጥሩ ግንዛቤ ያገኘ ስው

ሀ. ለስባቱ አብያተ ክርስቲያናት በተጻፈው መልእክት ውስጥ የተስጡት ብዙዎቹ ማስጠንቀቂያዎችና ትእዛዞች ባሬም በአማኞች ሕይወት ተግባራዊ ሊሆኑ እንደሚችሉ ይረዳል።
ለ. የራዕይ ትንቢቶች የተሰጡት በተምሳሌታዊ ቋንቋ በመሆኑ እውነተኛ ስዎችን ወይም ድርጊቶችን የሚጠቅሱ እንዳልሆኑ ያውቃል።
ሐ. የዮሐንስ ራዕይ መጽሐፍ ይዘት ስደትና መከራ ላልደረስባቸው ክርስቲ ያኖች ብዙም ቁም ነገር እንደሌለው ያውቃል።

መ. የዮሐንስ ራዕይ መጽሐፍ ክርስቲያኖች ሁሉ ሊያውቁት የሚገባ ስለ ክርስቶስና ስለ ፍጹም ድል አድራጊነት እውነቶችን መያዙን ይገነዘባል።

አዲስ ኪዳንና መላው መጽሐፍ ቅዱስ የሚዘጋው የድልና የማስጠንቀቂያ ማስታወሻ መልእክት በማቅረብ ነው። ስለ እኛ ድል አድራጊነት ጎላ አድርጎ ሥዕላዊ መግለጫ ያቀርባል። በራዕ 22:20 ላይ "በቶሎ እመጣለሁ" በማለት ሲናገር የስማውን የመጨረሻ ቃላት አስፍሯል። ይህን ጥናታችንን ስንጨርስ የዮሐንስ ራዕይ ላቀረበው መልእክት ተገቢውን ትኩረት ስለሰጠት፣ ወንጌልን ለዓለም ሁሉ ስላዳረሰና በታማኝነት እርሱን እያገለገልን ስላፈጸሙት ትንቢታዊ ድርጊቶች ራሳችንን እናዘጋጅ።

የመከራ ፈተና

1. አዛምድ፡- ቁጥሩን በተሰጠው ስፍራ በመጻፍ ከመጽሐፉ ወይም ከመልእክቱ ጋር አብሮ የሚሄደውን አመልክት።

1. 2ኛ ጴጥሮስ	4. 2ኛ ዮሐንስ
2. ይሁዳ	5. 3ኛ ዮሐንስ
3. 1ኛ ዮሐንስ	6. የዮሐንስ ራዕይ

___ሀ. ክርስቲያን ወንድሞችን በመርዳቱ ጋይዮስን የሚያመሰግን።
___ለ. ርእሱ ዋስትና ለአማኞች የሆነ መልእክት
___ሐ. በእቡቀለምሲስ የአገሳለጽ ስልት የተጻፈ
___መ. ክህደትን መዋጋት የሚል ርዕስ ያለው
___ሠ. እንግዶችን ስለ መቀበል የሚናገር
___ረ. በአንዳንድ መንገድ ይዘቱ ከይሁዳ መልእክት ጋር የሚመሳሰል
___ሰ. ስለ ድል አድራጊው ክርስቶስ የሚናገር
___ሸ. ለአማኞች የዘላለም ሕይወት ዋስትና ለመስጠትና የክርስቶስን በሥጋ መገለጥ የሚክዱትን ስመቃወም የተጻፈ
___ቀ. ስለ እውነተኛ ክርስቲያናዊ እውቀት የሚናገር
___በ. በእውነትና በፍቅር ስለመመላለስ የሚናገር
___ተ. የሐሰት መምህራንን እንዳትቀበል የተመረጠችዋን እመቤት የሚያስጠነቅቅ

2. አዛምድ፡- ቁጥሩን በክፍቱ ቦታ በመጻፍ ከመግለጫው ጋር አብሮ የሚሄደውን አመልክት።

1) ይሁዳ 2) 3ኛ ዮሐንስ 3) የዮሐንስ ራዕይ

__ሀ. በእስያ በሰባቱ አብያተ ክርስቲያናት ውስጥ ላሉት አማኞች የተጻፈ ሲሆን፣ አንዳንዶቹ ስመንፈሳዊ ሕይወታቸው ግዴለሾችና ቸልተኞች ሲሆኑ፣ ሌሎቹ ደግሞ በስደትና በስማዕትነት መከራ ይቀበሉ ነበር።
__ለ. የክርስቶስን ፍጹም አምላክነትና ፍጹም ሰው መሆን ለካዱ የሐሰት መምህራን የተጋለጡ፣
__ሐ. ክርስቶስን ከካዱና በመካከላቸው ስርገው ከገቡ ሐሰተኛ መምህራን እንዲጠነቀቁ ምክር የሚያስፈልጋቸው
__መ. አንደ አምላክ እንዲሰገድለት ያስገድድ በነበረው በሮማዊው ንጉሥ ዶሜቲያን ዘመን የኖሩ አማኞች፣

ምርጫ፡ ፊደሉን በመክበብ አብሮ የሚሄደውን አመልክት።

3. ለአዲስ አማኞች መሠረታዊ እውነቶችን ለማስተማር ብትፈልግ ለጥናታችሁ በይበልጥ ተስማሚ የሚሆነው መጽሐፍ፡-

ሀ. 2ኛ ጴጥሮስ ሐ. 3ኛ ዮሐንስ
ለ. 1ኛ ዮሐንስ መ. የዮሐንስ ራዕይ

4. የዮሐንስ ራዕይ ትንቢቶች ከሌሎቹ የመጽሐፍ ቅዱስ ትንቢቶች ጋር በቀላሉ እንዲለማማ የሚፈቅደው አመለካከት፡

ሀ. ወቅታዊ አመለካከት
ለ. ታሪካዊ አመለካከት
ሐ. ሃሳባዊ አመለካከት
መ. ትንቢታዊ አመለካከት

5. ስለ ሐሰት መምህራንና ስለሚጠብቃቸው ቅጣት መግለጫ የሚለጠው መልእክት፡-

ሀ. 2ኛ ዮሐንስ
ለ. 3ኛ ዮሐንስ
ሐ. የይሁዳ መልእክት

6. በራዕ1:12-13 ላይ ዮሐንስ በስባት የወርቅ መቅረዞች መካከል ክርስቶስን አንዳየ ይናገራል። ይህ፡-

ሀ. የአቡቀለምሲስ ተምሳሌት ነው።
ለ. እጥፍ ተፈጻሚነት ያለው ትንቢት ምሳሌ ነው።
ሐ. የታሪካዊ አጻጻፍ ምሳሌ ነው።

7. የዮሐንስ ራዕይ ትንቢቶች አብዛኛዎቹ ለመረዳት የሚያስቸግሩ የሆኑበት፡-

ሀ. እግዚአብሔር በግልጽ እንድንረዳቸው ስላልፈለገ ነው።
ለ. የሚፈጸሙበት ጊዜ ገና ስለሆነ ነው።
ሐ. ከብዙ መቶ ዓመታት በፊት የተጻፉ በመሆናቸው ነው።
መ. በትንሿ እስያ ለነበሩ አማኞች የተጻፉ በመሆናቸው ነው።

8. ቅደም-ተከተል፡- የሚከተሉትን ድርጊቶች በታሪካዊ ቅደም ተከተላቸው መሠረት አበቀምጥ። ቅድሚያ ላለው ድርጊት "1" ቁጥር በመጻፍ ተከታይ ለሆነው ድርጊት ደግሞ " 2" ጽፈህ አመልክት፡-

ሀ. ሐዋርያው ዮሐንስ ዮሐንስ ራዕይ የተባለውን መጽሐፍ ጻፈ።
ለ. ኢየሩሳሌም ወደቀች ቤተ መቅደሱም ፈረሰ።
ሐ. ሐዋርያው ዮሐንስ ወደ ፍጥሞ ደሴት ተሰዶ ሄደ።
መ. ኔሮ ሮምን አቃጥሎ በክርስቲያኖች አመካኘ።

የጥናት ማጠናከሪያ ጥያቄ መልሶች

9. ከእነርሱ ጋር ለእውነት አብረው ይሰራሉ። (መልስህ ከዚህ ጋር ተመሳሳይ መሆን አለበት)።

1. ሐ

10. ኢየሩሳሌም፣ ፍጥሞ፣ ኤፌሶን፣ ጥላቻ፣ እንደ አምላክ እንዲከገድሉት።

2. በአይናችን አይተን፣ ትንቢታዊ ቃል፣ በእግዚአብሔር

11. ሀ. የዛፉ ቅጠሎች ሕዝቡን እንደሚፈውሱ ተናገረ።
ለ. የራስህን መልስ ስጥ። ለዚህ ልዩነት ምክንያቱ ክርስቶስ የሕዝቡን ኃጢአት ስላስወገደና ለእነርሱ የሕይወትን ዛፍ ስላስገኘ።

3. ሀ

12. ለ እና ሐ

4. ሀ. የገቡት ቮልከው ነበር።
ለ. በሴሰኝነት
ሐ. ኢየሱስ ክርስቶስን
መ. የእግዚአብሔርን ሥልጣን
ሠ. ስለራሳቸው
ረ. መንፈስ ቅዱስ

13. ሀ. ድል ለሚነሣው (2:7፣11፣17-26፣ 3:5፣ 12፣ 21)
ለ. የተገባው ስለሆነ ምክንያቱም በለታሪደና በደሙ ለምችን ለእግዚአ ብሔር በመዋጀቱ (5:9)
ሐ. እንድ (20:1-3)
መ. ወደ ቅድስቲቱ ከተማ ሊገባ የሚችል ስሙ በሕይወት መጽሐፍ ተጽፎ የተገኘ ነው (21:27)።

5. ሀ. 3) ለቅዱሳን የተሰጠ አምነት (ቁ. 3)
ለ. 5) የሐዋርያት ትንቢት (ቁ. 17)
ሐ. 1) መንፈስ ቅዱስ (ቁ. 20)
መ. 4) የእግዚአብሔር ፍቅር (ቁ. 21)
ሠ. 2) የሚጠራጠሩ ለምች (ቁ. 22-23)

14. ሀ. 3
ለ. 1
ሐ. 4
መ. 2
ሠ. 4

6.

ጥቅሶች	የሚስጡት እውነት	የሚቃወሙት ስህተት
1፡1-3	ምሳሌውን ተመልከት	1
2፡22	ኢየሱስ ክርስቶስ መሆኑን ውሸተኞች ይክዳሉ።	2
3፡23	በእግዚአብሔር ልጅ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ማመን አለብን።	2
4፡1-3	ከእግዚአብሔር የሆነው መንፈስ የሚናገረው ኢየሱስ በሥጋ መምጣቱን ነው።	1
4፡15	እርሱ የሚኖረው ኢየሱስ ክርስቶስ የእርሱ ልጅ መሆኑን በሚያምኑ ሰዎች ውስጥ ነው።	2

15. ሐ

7. ሀ. ሐሰት ሰ. እውነት ሐ. ሐበት

16. መ

8. አይደሰም። እማኞች ክርስቶስን የሚክዱትን የሐሰት መምህራንን መቀበልና ማስተናገድ የሰባቸውም።

17. ሀ እና መ

10 ትምህርት

በአዲስ ኪዳን ላይ እንታመናለን

(አጠቃላይ መግለጫ)

ባለፉት ዘጠኝ ተከታታይ ክፍለ ትምህርቶች ስለ አዲስ ኪዳን መጻሕፍት ብዙ ጠቃሚ ነገሮችን ተምረናል። በዘመኑ ስለነበረው የፖለቲካ፣ የሃይማኖት እንደዚሁም የባህል ሁኔታዎች ምን ይመስሉ እንደነበር በመጠኑ በመዳሰስ፣ የአዲስ ኪዳንን መጻሕፍት ስለጻፉ ሰዎችና መጻሕፍቱ የተጻፉባቸውን ዓላማዎች እንድ በእንድ ተመልክተናል።

አሁንም ቢሆን መልስ ሊሰጣቸው የሚያስፈልጉ አንዳንድ ጥያቄዎች አሉ። ለምሳሌ ያህል አዲስ ኪዳን ሌሎችን ሳይጨምር ያጠናናቸው ሃያ ሰባቱን መጻሕፍት ብቻ ሰምን ያዘ? እነዚህ መጻሕፍት ወደ እኛ የተላለፉት እንዴት ነበር? ከ1800 ዓመታት በፊት በተጻፉበት ጊዜ እንደነበሩት ዛሬም በዚያው መልክ መኖራቸውን የሚያሳይ ምን ማስረጃ አለ?

ለእነዚህና እነዚህን ሰመሳሰሉት ጥያቄዎች መልስ የምናገኘው በዚህ በማጠቃለያው መግለጫ ላይ ነው። የአዲስ ኪዳን መጻሕፍት እንዴት ተስባስበው በዚህ መልክ እንደቀረቡ በመገንዘብ በትክክል ወደ እኛ ለመተላለፋቸው ከተሰጠው ማስረጃ ለመረዳት እንችላለን። ስለዚህም በእውነት በአዲስ ኪዳን ሰምን በእርግጠኝነት ልንታመን እንደምንችል እንድናስተውል ያደርገናል።

መንፈስ ቅዱስ የአዲስ ኪዳን መጻሕፍትን የጻፉትን ሰዎች መምራት ብቻ ሳይሆን፣ መጻሕፍቱን መልክ በማስያዝ ከትውልድ ወደ ትውልድ እንዲተላለፍ እንድታደርግ ቤተ ክርስቲያንንም ረድቷል። እኛ አዲስ ኪዳንን እንደ እግዚአብሔር ቃል አድርገን ለምን ልንታመንበት እንደምንችል በጥልቀት እንድንገነዘብ የሚረዳን መንፈስ ቅዱስ ጸሐፊዎቹንም ሆነ ቤተ ክርስቲያንን መምራቱን ስናረጋግጥ ነው።

የመንፈስ ቅዱስ ሥራ

አዲስ ኪዳን እንደ አንድ መጽሐፍ ሆኖ በመጠረዝ መልክ ሊይዝ የቻለው እያንዳንዱ የአዲስ ኪዳን መጽሐፍ ለየብቻ ከተጻፈ ከብዙ ዓመታት በኋላ ነበር። መጻሕፍቱ በተናጠል በየአብያተ ክርስቲያናቱ ተሰራጭተው ከቆዩ በኋላ ተሰባስበው እንደ አንድ መጽሐፍ የቤተክርስቲያን መሪዎች ሲጠቀሙበትና ሲገለገሉበት ቆይተው በመጨረሻ በቤተ ክርስቲያን ጉባኤ ታውቆ በይፋ ጸደቀ።

በቅዱሳን ሰዎች ተጻፈ

ክርስቶስ ወደ ሰማይ ካረገ በኋላ እንዳንድ ሰዎች አዲስ ኪዳን ብለን የምንጠራውን መጽሐፍ እንዲጽፉ እግዚአብሔር በመንፈሱ መራቸው። በመጀመሪያ ሐዋርያት ከክርስቶስ ጋር የነበራቸውን የመጀመሪያ ልምምድ ለሰዎች በማስተማር እርሱ የብሉይ ኪዳን ትንቢቶችን እንዴት እንደፈጸመ አሳዩ (የሐዋ 2:14-40፤ 3:17-26፣ 7:2-53፤ 8:26-35)። ከዚያም በኋላ ጳውሎስና ጴጥሮስ እንደዚሁም ሌሎቹ በቃል የሰበኩትንና ያስተማሩትን በጽሑፍ በማድረግ በየስፍራው ለነበሩ አብያተ ክርስቲያናትና ግለሰቦች መልእክቶችን ላኩ። በኋላም አማኞች ስለ ኢየሱስ ሕይወትና ስላስተማራቸው ትምህርቶች ትክክለኛ የሆነ መረጃ እንዲኖራቸው ማቴዎስ፣ ማርቆስ፣ ሉቃስና ዮሐንስ አራቱን ወንጌላት ጻፉ። በመጨረሻም ዮሐንስ ወደፊት ስለሚፈጸሙት ነገሮች እግዚአብሔር በገለጠለት መሠረት፣ የተቀበለውን ራዕይ እንዲጽፍ ተነገረው (ራዕ1:1፣11)። በጠቅላላው ሃያ ለባቱ የአዲስ ኪዳን መጻሕፍት ከ49 - 95 ዓ.ም በነበሩት ዓመታት ውስጥ ተጠናቀው ቀረቡ።

በምዕመናን በኩል በአንድ ላይ ተሰባሰቡ

በዚያን ወቅት አብያተ ክርስቲያናት የተላኩላቸውን መልእክቶች እየተለዋወጡ ይገለገሉባቸው እንደ ነበር በቆላ 4:16 ላይ የተጻፈው ቃል ሲገልጽ "ይህችም መልእክት በእናንተ ዘንድ ከተነበበች በኋላ፣ በሎዶቅያ ሰዎች ማኅበር ደግሞ እንድትነበብ እድርጉ፣ በሎዶቅያም የምትገኘውን መልእክት እናንተ ደግሞ አንብቡ" በማለት ይናገራል። በዚያ ወቅት የመልእክቶቹ ቅጅዎች በእጅ እየተገለበጡ ነበር እየተባዙ ይሄዱ የነበሩት።

መጻሕፍቱ በተናጠል በየአብያተ ክርስቲያናቱ ከተሰራጩ በኋላ እንዳያቸውን በአንድ ላይ ማሰባሰብ ተጀመረ። ጴጥሮስ ስለ ተሰባሰቡት የጳውሎስ መልእክቶች በ2ጴጥ 3:15-16 ላይ ይናገራል። በዚህ መንገድ የጳውሎስ መልእክቶች በአንድ ላይ ተሰባስበው በመጽሐፍ መልክ ተጠርዘው ተገኝተዋል። በተጨማሪም አራቱ ወንጌላት ብዙ ጊዜ በአንድ ላይ ተጠርዘው ተገኝተዋል። የሐዋርያት ሥራ መጽሐፍም እንዳንድ ጊዜ ከነዚህ ጋር አብሮ ይገኛል። መጻሕፍቱ ተጽፈው ካለቁ በኋላ የማሰባሰቡ ሂደት በተመሰላይ መንገድ በመቀጠል የአዲስ ኪዳን መጻሕፍት በሙሉ በአንድ

ላይ ለመሆን በቁ። በ4ኛው መቶ ዓመት የተገኘው ጠቃሚ የመጽሐፉ ስብስብ ጠቅላላውን የአዲስ ኪዳን መጻሕፍት የያዘ ነበር።

የቤተክርስቲያን መሪዎች አጸደቁ

የአዲስ ኪዳን መጻሕፍትን የተቀበሉ ሰዎች የእግዚአብሔር ቃል እድርገው ነበር የተቀበሉአቸው። ከ2ጴጥ 3:15-16 ላይ ቀደም ሲል እንደተመለከትነው፣ ጴጥሮስ ጳውሎስ የጻፈውን መልእክት እንደ እግዚአብሔር ቃል ነበር የቆጠረው። በ1ጢሞ 5:18 ላይ ጳውሎስ ቅዱሳት መጻሕፍት በሚለው ቃል የጠቀሳቸው "የሚያበራየውን በሬ አፉን አትሰር" ደግሞም "ለሠራተኛ ደሞዙ ይገባዋል" የሚሉት የዘዳግምና (25:4) የሉቃስ ወንጌል (10:7) መጽሐፍት ናቸው። ከብሉይም ሆነ ከአዲስ ኪዳን በመጥቀስ ቅዱሳት መጽሐፍት ብሎ ይጠራቸዋል። ይህም በቀጥታ የሚያመለክተው "የእግዚአብሔር ቃል" የሆነውን መጽሐፍ ቅዱስን ነው። ጳውሎስና ዮሐንስም በብሉይ ኪዳን ዘመን ቅዱሳት መጻሕፍት በምኩራብ ይነበቡ እንደነበረው ልማድ በቤተክርስቲያንም መልእክቶቻቸው እንዲነበቡላቸው እንደፈለጉ እንመለከታለን (1ኛ ተሰ 5: 27፣ ቆላ 4:16፤ራዕ 1:3)።

የአዲስ ኪዳን መጻሕፍት ተጽፈው በተሰራጩበት ዓመታት፣ በተለያዩ ስፍራዎች የቤተክርስቲያን መሪዎች የእግዚአብሔር ቃል መሆናቸውን በመረዳት፣ ለብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ይሰጥ ከነበረው ክብር ጋር እኩል ክብር በመስጠት በጽሑፋቸው ከተለያዩ የአዲስ ኪዳን መጻሕፍት ይጠቅሱ ነበር።

የአዲስ ኪዳን መጻሕፍትን እየጠቀሱ ይጠቀሙ የነበሩ የቤተ ክርስቲያን አባቶች

ስምና ጊዜ	ቦታ	የተጠቀሙት መጻሕፍት
የሮሙ ክሌመንት (30-100) ዓ.ም.	ሮም	ማቴዎስ፣ ሮሜ፣ 1ቆሮ፣ ዕብራውያን
ፖሊካርፕ (69-155) ዓ.ም.	ስምርና	ማቴዎስ፣ ሐዋ.፣ የጳውሎስ መልዕክቶች፣ 1ጴጥ፣ 1ዮሐ
ፓፕያስ (80-155) ዓ.ም.	ሄራፖሊስ	ማቴዎስ፣ ማርቆስ፣ ዮሐንስ፣ 1ዮሐንስ፣ 1ጴጥሮስ
ጀስቲን ማርቲር (100-165) ዓ.ም.	ሮም	ወንጌላት፣ ሐዋ፣ 1ጴጥ፣ ሮም፣ 1ቆሮ፣ ገላ፣ ኤፌ፣ ቆላስያስ፣ 2ተሰ፣ ዕብራውያን፣ ራዕይ
ኢራኒዮስ (140-203) ዓ.ም.	ትንሿ እስያ፣ ጎል	ሁሉም የአዲስ ኪዳን መጻሕፍት፣ ከፊልሞናና ከ3ዮሐ በስተቀር።
ተርቱልያን (150-222) ዓ.ም.	ካርቴጅ	ሁሉም የአዲስ ኪዳን መጻሕፍት፣ ከፊልሞና፣ ከያዕቆብ መልዕክትና ከ2 እና 3ዮሐ በስተቀር
ታቲያን	ሶሪያ፣ ሮም	አብዛኞቹን የአዲስ ኪዳን መጻሕፍት

(170) ዓ.ም.		
ቴዎፍሎስ (115-188)	አንጾኪያ	አብዛኞቹን የአዲስ ኪዳን መጻሕፍት
ክሌሜንት (155-215)	እስክንድርያ	ሁሉም የአዲስ ኪዳን መጻሕፍት፣ ከያዕቆብ መልዕክት፣ ከ2ጴጥ፣ ከ3ዮሐ በስተቀር
ኦሪገን (185-253)	እስክንድርያ	ሁሉም የአዲስ ኪዳን መጻሕፍት፣ ከ2ና 3ዮሐ መልዕክት በስተቀር
ዲዮኒሰስ	እስክንድርያ	ሁሉም የአዲስ ኪዳን መጻሕፍት፣ ከ2ጴጥና ይሁዳ በስተቀር

በሠንጠረዡ ላይ የተጠቀሱት የቤተ ክርስቲያን አባቶች ከአዲስ ኪዳን መጻሕፍት መጥቀስ ብቻ ሳይሆን፣ የሐሰት አስተማሪዎችን ለመቃወም እነዚህን የአዲስ ኪዳን መጻሕፍት እንደማስረጃ ይጠቀሙ ነበር። ለምሳሌ ኢራንዩስና ኦሪገን የኖስቲሲዝምን ትምህርት ስህተት በማሳየት ሲቃወሙ በአዲስ ኪዳን መጻሕፍት ላይ ተመሥርተው ነበር። (በከፍለ ትምህርት 9 ላይ የ1 ዮሐንስ መልዕክት የተጻፈው የዚህ ትምህርት ጅማሬ ላይ እንደነበረና፣ መንፈስ መልካም ነው ቁስ አካል ግን ክፉ ነው የሚለውን የኖስቲሲዝም ትምህርት ለመቃወም እንደነበረ ማንነታችንን አስታውስ።) እነዚህ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች አዲስ ኪዳንን በዚህ መልክ መጠቀማቸው ለመጻሕፍቱ የነበራቸውን ታላቅ ክብር ያሳያል።

በቤተክርስቲያን ጉባኤ ጸደቀ

ከዚህ ጋር ልናይ የሚገባን ጉዳይ የአዲስ ኪዳን ጥራዝን ስመወሰን የአብያተ ክርስቲያናት መሪዎች ስብስባ አስፈላጊ ሆኖ እንደነበረ ነው። ይህ ደግሞ እስከ አራተኛው መቶ ክፍለ ዘመን መዝጊያ ድረስ ሊካሄድ አልተቻለም ነበር። የተለያዩ የቤተ ክርስቲያን ጉባኤዎች በተለያዩ ስፍራዎች ተከናውነው ነበር። የኒቂያ ጉባኤ በ (325 ዓ.ም.)፣ የሎዶቂያ ጉባኤ በ (363 ዓ.ም.) የደማሲያን ጉባኤ በ (382 ዓ.ም.) ተከናውነው ነበር። በአዲስ ኪዳን ቃኖና ላይ በጣም አስፈላጊ ክንዋኔ የተከናወነው በካርቴጁ ጉባኤ ነው። የካርቴጁ ጉባኤ በ397 ዓ.ም. ተደረገ። ይህ ጉባኤ እንደሎዶቅያው ጉባኤ ያለ ሃሳብ በመያዝና አንድ እርምጃ ወደፊት በመሄድ በጥራዙ ዕቅካተት የሚገባቸውን መጽሐፍት ዝርዝር አውጥቶ ያሁኑን የአዲስ ኪዳን ጥራዝ አጸደቀ።

በዚሁ በአራተኛው ክፍለ ዘመን መጨረሻ ላይ እነዚህ በእግዚአብሔር መንፈስ መሪነት በቅዱሳን ሰዎች ተጽፈው ለብዙ ዘመናት አገልግሎት ላይ የዋሉት መጻሕፍት እንደ ቅዱሳት መጻሕፍት ተቆጥረው በእግዚአብሔር ቃልነት እንዲወሰዱ በቤተክርስቲያን ጉባኤ ጸደቀ። በጉባኤው የጸደቁ ቅዱሳት መጻሕፍት፣ የእግዚአብሔር ሥልጣናዊ ቃል፣ ቃኖናዊ መጻሕፍት (The Conon of Scripture) ተብለው እንዲታወቁ ተደርገዋል። የመጻሕፍቱ በይፋ መታወቅ ያስፈለገበት ሦስት ምክንያቶች ነበሩ።

የመጀመርያው፦ ሌሎች መጻሕፍት መታየት ስለጀመሩና ሰዎች እንደ እግዚአብሔር ቃል እድርገው በመቀበላቸው ነበር። ቤተ ክርስቲያን በተወለደችባቸው የመጀመርያዎቹ 150 ዓመታት ውስጥ ስለ ክርስቶስና ስለ ደቀመዛሙርቱ የተጻፉት መጽሐፍት 27ቱ የአዲስ ኪዳን መጻሕፍት ብቻ እልነበሩም። ሉቃስ በወንጌሉ መግቢያ ላይ ሌሎች ብዙዎች እንደተጻፉ ጠቅሷል (1፡1)። ጳውሎስም ስለጌታ ቀን እርሱ ከተናገረው ጋር የሚቃረን ምንም ዓይነት ሌላ ጽሑፍ ቢደርሳቸው እንዳይቀበሉ የተሰሎንቄን ቤተክርስቲያን ሰዎች አስጠንቅቋቸዋል (2ተሰ 2፡2)።

ሁለተኛው፦ ማርሲዮን የተባሰ ስው ነደሉ የሆነ የአዲስ ኪዳን መጻሕፍት ዝርዝር በማቅረቡና ሰዎችም ይህን መቀበል ስሰ ጀመሩ ነበር። ማርሲዮን፥ የማይፈልጋቸውን መጻሕፍት በማውጣት የሉቃስ ወንጌልንና አሥር የጳውሎስ መልእክቶችን ብቻ ያስቀረ የሐሰት አስተማሪ ነበር። ሌሎች መሪዎች የእግዚአብሔር ቃል አድርገው የተቀበሏቸውን ብዙ መጻሕፍት አልተቀበለም። ስለዚህም የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ማርሲዮን የስረዛቸውን መጻሕፍት ስልጣን ማረጋገጥና ማጽደቅ ነበረባቸው።

ሦስተኛው፦ በ303 ዓ.ም. የሮም ንጉሥ ዳዮክሌሽያን የሃይማኖት መጻሕፍትን እየፈለገ ሲያቃጥል ቤተክርስቲያን የትኞቹን መጻሕፍት መጠበቅና መደበቅ እንዳሰባቸው መወሰን ግድ ስለሆነ ነበር። በዚህ ምክንያት የቤተክርስቲያን መሪዎች ሊደበቁና ሊጠበቁ የሚገባቸው መጻሕፍት የትኞቹ እንደሆኑ ለማስታወቅ ይፋዊ መግለጫ መስጠት ነበረባቸው።

አሁን በእጃችን ያሉት 27 የአዲስ ኪዳን መጻሕፍት እንደ እግዚአብሔር ቃል ያጸደቀው በ397 ዓ.ም. የተሰበሰበው የካርቴጅ ጉባኤ ነበር። በአዲስ ኪዳን ውስጥ የተጠቃለለው እያንዳንዱ መጽሐፍ የሚከተሉትን መመዘኛዎች ማሟላት ነበረበት። የአዲስ ኪዳን መጻሕፍት ተሰባስበው ከመጠረዛቸው በፊት ለጥራዝ የሚበቁትን መጻሕፍት ለመወሰን መመዘኛ ወጥቶላቸዋል። ይህም በግሪክ "ካኖን" ከሚል ቃል የመጣ ሃሳብ ነው። "ካኖን" መስኪያ ማለት ነው።

1. *ሐዋርያዊነት*፦ የመጽሐፉ ጸሐፊ ሐዋርያ መሆን አለበት ወይም ከሐዋርያት ጋር የቅርብ ግንኙነት ያለው ስው ሊሆን ይገባል። ትምህርቱም ከሐዋርያት ትምህርት ጋር መስማማት ነበረበት።
2. *መንፈሳዊነት*፦ በክርስቶስ ማንነትና እርሱ ባከናወናቸው ሥራዎች ላይ የተመሠረተ ከፍተኛ መንፈሳዊ ባሕርይና ሥነ ምግባር የሚያንጸባርቅ ሊሆን ይገባል።
3. *ዓለም አቀፋዊነት*፦ በጠቅላላው በቤተክርስቲያን ተቀባይነት ያለው መሆን ነበረበት።
4. *የመንፈስ ቅዱስ ምሪት*፦ (Inspiration) በመንፈስ ቅዱስ አነሳሽነትና ምሪት ስመጻፉ የማያሳስት ማረጋገጫ ሊሰጥ የሚችል መሆን

አስበት። 2ጢሞ 3፡16፣ 12 እግዚአብሔር በመንፈሱ ገልጦ ስጽሑፍ ያስቀረልን የእርሱ ቃል መሆን አለበት።

ጥንታውያን ስዎች ለሥነ - ጽሑፍ እንደወረቀት ይገለገሉባቸው የነበሩት ተከሉች፣ የእንስሳ ቆዳ ጥቅሎችና ብራናዎች ነበሩ። ቅዱሳት መጻሕፍትም በእጅ ይጻፉ የነበሩት በእነዚህ ላይ ነበር። በዚህ ሁሉ ግን እንደ መጽሐፍ ቅዱስ በደንብ ተጠብቆ ከትውልድ ወደ ትውልድ የተላለፈ ጽሑፍ የለም። አዲስ ኪዳን ለ1400 ዓመታት የቆየውና ከትውልድ ወደ ትውልድ የተላለፈው በጥራዝ መልክ ነበር። እነዚህም ጥራዞች ስትልልቅ አብያተ ክርስቲያናት፣ በአንዳንድ ገዳማትና በጥቂት ሀብታም ስዎች ቤት ውስጥ ብቻ ይገኙ ነበር። ነገር ግን በ1437 የመጀመሪያው የህትመት መሣሪያ በተፈለሰፈበት ወቅት ሁኔታው ፍጹም ተለወጠ። በ1456 እ.አ.አ በማተሚያ መሣሪያ የመጀመሪያ መጽሐፍ በመሆን ታተመ። ከዚያ በፊት ግን በእጅ እየተገለበጠ አድካሚ በሆነ መንገድ ይዘጋጅ ነበር። የማተሚያ መሣሪያ ከተፈለሰፈ በኋላ ግን በእጅ የመገልበጡ ሥራ ተቃለለ። ስለዚህም እያንዳንዱ ስው የራሱ መጽሐፍ ቅዱስ ሊኖረው ቻለ።

ዛሬ እያነበብን የምንገለገልበት አዲስ ኪዳን የብዙ ታማኝ ክርስቲያኖች ልፋትና ድካም ውጤት ነው። መንፈስ ቅዱስ እንዳነሳሳቸው የጸፉ ስዎች፣ በጥንቃቄ ገልብጠውና ጠብቀው ለእኛ ያስተላለፉልን ቅዱሳንና በሚገባን መንገድ አዲሱን ትርጓሜ ያዘጋጁ ምሁራን እንደዚሁም ወደ እያንዳንዳችን ቋንቋ ተርጉመው ያቀረቡልን ስዎች ሁሉ ስለጥረታቸውና ልፋታቸው ሊመሰገኑ ይገባል።

ይህን የመድኃኒታችንን የኢየሱስ ክርስቶስን መንግሥት፣ ኃይልና ክብር የሚያውጀውን አዲስ ኪዳን፣ ስዚህ መልኩ ስእኛችን ማግኘት መታደልና መባረክ ነው። ስለሆነም በትጋት በማጥናትና መልእክቱን ከሕይወታችን ጋር ስማዋሃድ ሕይወትን የሚለውጥ የእግዚአብሔር ቃል መሆኑን እምነን ስሌሎች ማዳረስ አለብን።

የሙከራ ፈተና መልሶች

ክፍለ ትምህርት አንድ

1. ሀ. በሮማውያን ኃይል ምክንያት ስአካባቢው በሙሉ ሰላምና ጸጥታ ስመኖሩ እንደልብ መዘዋወርና መገናኘት ይቻል ነበር።
   ለ. በግሪክ ባህል መስፋፋት ምክንያት በግሪክ ቋንቋ ስየትም ስፍራ ይጠቀሙበት ነበር።
   ሐ. ስለሚመጣው መሲሕ የተነገሩት ትንቢቶች በብዙ ስፍራዎች የተጠኑትና የታወቁት በአይሁድ ሃይማኖትና በአይሁዳውያን በየስፍራው መበተን ምክንያት ነበር።
   መ. የተለያዩ ሃይማኖቶች መኖራቸው ስዎች በተለያዩ መንገዶች መንፈሳዊ እርዳታና እርካታ ለማግኘት ይሞክሩ እንደነበር የሚያመለክት ነው።

2. ሀ. 3) ምኩራብ
   ለ. 4) ሴፕቲዩጀንት
   ሐ. 1) እውግስጦስ ቄሳር
   መ. 7) ስዱቃውያን
   ሠ. 2) ታላቁ እስክንድር
   ረ. 9) የፋሲካ በዓል
   ስ. 10) ታላቁ ሄሮድስ
   ሸ. 6) ፈሪሳውያን
   ቀ. 8) በዓለ ሃምሳ
   በ. 5) የአይሁድ ሸንጎ
   ተ. 13) ፕሮሴላይት
   ቸ. 12) ዲያስፓራ
   ፕ. 11) ሄለኒስት

3. ሀ. ገርዝር ድርጊቶችና ሐቆችን
   ለ. ስለ ክርስቶስና ስለ ክርስቲያን ሕይወት የተስጡ እውነቶች
   ሐ. ስለ ቤተክርስቲያን አመራርና ስለ ሌላም ጉዳዮች ለአንድ ግለሰብ የተስጡ መመሪያዎች
   መ. ስለ አሁኑና ስለ ወደፊቱ መገለጥ የተስጡ መልእክቶች፣ (መልስህ ከዚህ ጋር ተመሳሳይ መሆን አለበት።)

4. ሀ. 2) ዮሐንስ
   ለ. 1) ሉቃስ
   ሐ. 4) ጳውሎስ
   መ. 2) ዮሐንስ
   ሠ. 4) ጳውሎስ
   ረ. 3) ያዕቆብ

5. ከ6ዓ.ዓ-29 ዓ.ም - ማቴዎስና ማርቆስ፡ የታሪክ መጻሕፍት
   ከ30 ዓ.ም - 60 ዓ.ም - የሐዋርያት ሥራ፡- የታሪክ መጽሐፍ
   - ሮሜ፡- የትምህርት መጽሐፍ
   - ገላትያ፡- የትምህርት መጽሐፍ
   - ፊልሞና፡- የግል ደብዳቤ መጽሐፍ
   ከ60-95 ዓ.ም - ዕብራውያን፡- የትምህርት መጽሐፍ
   - 1ኛና 2ኛ ጢሞቴዎስ፡- የግል ደብዳቤ
   - የዮሐንስ ራዕይ፡- የትንቢት መልእክት

ክፍለ ትምህርት ሁለት

1. ሐሰት
2. እውነት
3. ሐሰት
4. ሐሰት
5. እውነት
6. ሐሰት
7. ሐሰት
8. እውነት
9. እውነት
10. ሐሰት
11. ለ
12. ሐ
13. ሀ
14. መ
15. ሐ
16. ስማርያ
17. የኋለኛው አገልግሎትና ተቃውሞ
18. በቢታንያ
19. ይሁዳና ገሊላ
20. ከራሱ ጋር

ክፍለ ትምህርት ሦስት

1. እውነት
2. ሐሰት
3. ሐሰት
4. እውነት
5. ሐሰት
6. እውነት
7. እውነት
8. ሐሰት
9. ሐሰት
10. እውነት
11. ሐ
12. ሀ

13. ሀ. 2) ማርቆስ
ለ. 1) ማቴዎስ
ሐ. 1) ማቴዎስ
መ. 2) ማርቆስ
ሠ. 2) ማርቆስ

14. (በራስህ አባባል)

ሀ. ስህተቱ ዘንድ ተቀባይነት ያገኘበትና ዝናው የወጣበት ዘመን
ለ. ተቀባይነት ያጣበትና ተቃውሞ የደረሰበት ዘመን።

15. (በራስህ አባባል) በብሉይ ኪዳን ስለ መሲሁ የተነገሩት ትንቢቶች እንዴት በኢየሱስ ሕይወት እንደተፈጸሙ ያሳያል።

16. (በራስህ አባባል) የሰዎችን ችግር የፈታበት የኢየሱስ የኃይል አገልግሎት፡

17. "የእግዚአብሔር ልጅ የኢየሱስ ክርስቶስ ወንጌል *መጀመሪያ*" (1፡1)

ክፍለ ትምህርት አራት

1. ሀ. 1) ሉቃስ
ለ. 2) ዮሐንስ
ሐ. 2) ዮሐንስ
መ. 2) ዮሐንስ
ሠ. 1) ሉቃስ
ረ. 1) ሉቃስ
ሰ. 1) ሉቃስ

2. እውነት
3. ሐሰት
4. እውነት
5. እውነት
6. ሐሰት
7. ሐሰት

8. ለ

9. ሀ

ክፍለ ትምህርት አምስት

1. ምሳሌውን ተመልከት።

2. እውነት

3. ሐሰት፡ የሐዋርያት ሥራ የሚያሳየው ጳውሎስ ደጋግሞ ወደ አሕዛብ ዞር ያለው ብዙ አይሁዶች መልእክቱን ሰላልተቀበሉት እንደሆነ ነው።
4. እውነት

5. ሐሰት፡ ጳውሎስ ወደ ገላትያ ሰዎች መልእክት የጻፈው ስለ ድነት የሐሰት ትምህርት መቀበላቸውን ሰምቶ ምላሽ ለመስጠት ነበር።

6. ሀ. 5) ያዕቆብ
ለ. 1) ጴጥሮስ
ሐ. 3) ሉቃስ
መ. 4) የሐዋርያት ሥራ
ሠ. 3) ሉቃስ
ረ. 6) ገላትያ
ሰ. 1) ጴጥሮስ
ሸ. 2) ጳውሎስ

7. ሀ. 6 ሐ. 1 ሠ. 2 ሰ. 5
ስ. 4 መ. 3 ረ. 7

8. ሀ. ምሳሌውን ተመልከት
ለ. ቀርጤስ፣ 9
ሐ. መቄዶንያ፣ 2
መ. ቂሳርያ፣ 7
ሠ. ኢየሩሳሌም፣ 8
ረ. ኤፌሶን፣ 4
ሰ. ገላትያ፣ 5
ሸ. ሮም፣ 1
ቀ. ኢየሩሳሌም፣ 8
በ. ቆሮንቶስ፣ 3
ተ. ቀሬና፣ 10

ክፍለ ትምህርት ስድስት

1. ሀ. 5) ሮሜ
ለ. 4) 2ኛ ቆሮንቶስ
ሐ. 2) 2ኛ ተሰሎንቄ
መ. 5) ሮሜ
ሠ. 3) 1ኛ ቆሮንቶስ
ረ. 4) 2ኛ ቆሮንቶስ
ሰ. 2) 2ኛ ተሰሎንቄ
ሸ. 4) 2ኛ ቆሮንቶስ
ቀ. 5) ሮሜ
በ. 1) 1ኛ ተሰሎንቄ
ተ. 1) 1ኛ ተሰሎንቄ
ኾ. 3) 1ኛ ቆሮንቶስ
ነ. 3) 1ኛ ቆሮንቶስ

2. ሀ. ቆሮንቶስ
ለ. ተሰሎንቄ
ሐ. ሮም
መ. ቆሮንቶስ

3. ሀ. ስለ እግዚአብሔር ጽድቅ ወንጌል
ለ. ሥራ ፈትነት
ሐ. የቤተክርስቲያን ችግሮች ላይ
መ. በግል ሄዶ ሊያስተምራቸው ባለመቻሉ
ሠ. ስለ መታጎን ትንሣኤ

ክፍለ ትምህርት ስበት

1. ሀ. 2) ኤፌሶን
ለ. 3) ቆላስይስ
ሐ. 1) ፊልሞና
መ. 2) ኤፌሶን
ሠ. 4) ፊልጵስዩስ
ረ. 2) ኤፌሶን
ሰ. 4) ፊልጵስዩስ
ሸ. 3) ቆላስይስ
ቀ. 1) ፊልሞና
በ. 3) ቆላስይስ
ተ. 1) ፊልሞና
ቸ. 4) ፊሊጵስዩስ

2. ሐሰት። ሉቃስ ስለ ጳውሎስ መያዝና መታሰር የገለፀው ኃላፊ የክርስትና ሃይማኖት ለሮም መንግሥት የፖለቲካ ማስፈራሪያ እንዳልሆነ የሚያሳይ ነበር።

3. ሐሰት፡ የእሥር ቤት መልእክቶች የተባሉበት ምክንያት ጳውሎስ እሥር ቤት በነበረበት ወቅት ስለጻፋቸው ነው።

4. እውነት

5. ሐሰት፡ የፊልሞና መልእክት ጌታውን በማሳዘኑ ምክንያት ይቅርታ ለሚያስፈልገው ባሪያ ጳውሎስ ምን ያህል ያስብና ይገደው እንደነበር የሚያሳይ ነው፤

6. ሐሰት። ፊልጵ 2፡5-11 ከተጠቀሱት የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ጋር ጠቃሚነቱ የክርስቶስን አምላክነት በማረጋገጥ ሰው ሆኖ በመጣ ጊዜ ምን እንደተፈጸመ ለማወቅ እንድንችል ስለሚረዳን ነው።

7. እውነት

8. ሐሰት። የቆላስይስ ክርስቲያኖች የሐሰት ትምህርት መከተላቸውን እንዲያውቁ ለመርዳት የቀየሰው ዘዴ ስህተታቸውን በግልጽ ለማየት እንዲችሉ ስለ ክርስቶስ እውነቱን በማቅረብ ነበር።

ክፍለ ትምህርት ስምንት

1. ሀ. 2) 2ኛ ጢሞቴዎስ
ለ. 4) 1ኛ ጴጥሮስ
ሐ. 5) ዕብራውያን
መ. 1) 1ኛ ጢሞ
ሠ. 5) ዕብራውያን
ረ. 1) 1ኛ ጢሞቴዎስ
ሰ. 3) ቲቶ
ሸ. 4) 1ኛ ጴጥ
ቀ. 3) ቲቶ
በ. 5) ዕብራውያን
ተ. 2) 2ኛጢሞ

2. ሀ
3. ሐ
4. ሐ
5. ስ

6. ሀ. ቲቶ (2:1፣11)
ለ. 2ኛ ጢሞ (4:2፣7፣9)
ሐ. ዕብ (10:12)
መ. 1ኛ ጴጥ (4:16)
ሠ. 1ኛ ጢሞ (1:3)
ረ. ዕብ (2:3)

ክፍለ ትምህርት ዘጠኝ

1. ሀ. 5) 3ኛ ዮሐንስ
ለ. 3) 1ኛ ዮሐንስ
ሐ. 6) የዮሐንስ ራዕይ
መ. 2) ይሁዳ
ሠ. 5) 3ኛ ዮሐንስ
ረ. 1) 2ኛ ጴጥሮስ
ሰ. 6) የዮሐንስ ራዕይ
ሸ. 3) 1ኛ ዮሐንስ
ቀ. 1) 2ኛ ጴጥሮስ
በ. 4) 2ኛ ዮሐንስ
ተ. 4) 2ኛ ዮሐንስ

2. ሀ. 3) የዮሐንስ ራዕይ
ለ. 2) 3ኛ ዮሐንስ
ሐ. 1) ይሁዳ
መ. 3) የዮሐንስ ራዕይ

3. ስ
4. መ
5. ሐ
6. ሀ
7. ስ

8. ሀ. 4
ለ. 2
ሐ. 3
መ. 1

እስጀምሮ ላስጨረሰን ጌታ ከዘላለም እስከ ስዘላለም ድረስ ክብር ይሁን!! አሜን።